ጥናት አሥር - ምዕራፍ ዘጠኝ

ነፃነት

ነፃነት ማለት «የፈቀድነውን ነገር ማድረግ» ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር እንድንሠራ የሚፈልገውን ነገር እንዳንሠራ ከሚያግዱን ነገሮች ሁሉ መፈታት ማለት ነው። ብዙ ሰዎች ነፃነትና ሕገ ወጥነት ይምታታባቸዋል። ሆኖም ነፃነት በግልጽ የሚብራራው የእርሱ ተቃራኒ የሆነው ባርነት ሲታሰብ ነው። ተቀዳሚ ዋጋ የሚሰጠው የአዕምሮና የመንፈስ ነፃነት ነው።

ወደ ባርነትና ወደ ኃጢአት ውስጥ ከሚጨምረን ማናቸውም ነገር ነፃ እንድንወጣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ይህም እውነተኛ ነፃነት ነው። ይህንን ነፃነት ካላገኘን ወደድንም ጠላን ባርያዎች ነን። እኛ ይህንን ነፃነት እንድናገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ ስለምናውቅ በእርግጥ ያገኘነው መሆናችንን እስክናረጋግጥ ድረስ መፈለግ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር በምዕ. 9 ውስጥ ለሕዝቡ ተስፋ የሚሰጣቸው ይህንን ዓይነት ነፃነት ነው።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት ውስጥ እንዲገባ ከሚገፋፉት ከነዚህ ግፊቶች ነፃ እስካልወጣ ድረስ እግዚአብሔር ሊሰጠው የሚፈልገውን ሥጦታዎች ተቀብሎ ሊደሰት አይችልም። ይህ ነፃነት ከእግዚአብሔር ብቻ የሚገኝ መንፈሳዊ ሥጦታ ነው። ይህ አንድ ጊዜ ተቀብለነው በዚያው የሚያቆም ነገር አይደለም፥ «የሚያገሳው አንበሳ» ጠላታችን ዲያብሎስ ምንጊዜም ባሪያዎቹ ሊያደርገን ይጥራል። ስለዚህ ሳንፈራ፡-

«ምርኮህ አድርገኝ ጌታ ነፃ እወጣለሁ፤ ሰይፈንም አስጥለኝ ድል አድራጊ እሆናለሁ» እያልን ልንዘምር እንችላለን።

መሠረታዊ ነጥቦች

ምዕ. 9-14 በብዙ መንገዶች ከምዕ. 1-8 እንደሚለይ አዘውታሪ ላልሆነ አንባቢም እንኳ ስውር አይሆንም። ይሁን እንጂ ምዕ. 9-14 ከትንቢተ ዘካርያስ የማይነጠል ክፍል ከመሆኑ ሌላ ከብራናዎቹም ሆነ ከመጽሐፉ ከራሱ ምንም መረጃ አላገኘንም። ስለዚህ በሚቀጥለው ሁኔታ እንመለከታቸዋለን።

ምዕ. 1-8 ለኢየሩሣሌም ሕዝብ የተፃፈ መሆኑ ግልጽ ነው። ሊቀ ካህናቱ ኢያሱና የፋርስ ወረዳ የሆነችው የይሁዳ አስተዳዳሪ ዘሩባቤል በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል። ይሁንና ምዕ. 9-14ስ የተፃፈው ለማን ነበር? ይህ ክፍል ምናልባት በፋርስ ለቀሩት አይሁድ የተፃፈ ሊሆን ይችላል። ሁኔታው እንደዚህ ነው ካልን፡-1. ኢያሱና ዘሩባቤል ለምን እንዳልተጠቀሱ፤ 2. በርካታ አበይት ትምህርቶች ለምን እንደተደገሙና 3. አብዛኛው የመልዕክቱ ክፍል በምሳሌያዊ ወይም በስዕላዊ ቋንቋ ለምን አንደቀረበ ለማብራራት ያመቸናል።

ምናልባት እነዚህ ምዕራፎች ሦስት የአተረጓጎም ደረጃዎች ሊኖራቸው ይችላል፡-

ታሪካዊ	በነዚህ ሦስት አተረጓጎሞች
መሢሐዊ	ውስጥ ከእግዚአብሔር የተላከ መንፈሳዊ
ትንቢታዊ	መልእክት ይገኛል።

አንዳንድ ጥቅሶች አንድ ትርጉም ብቻ ይኖራቸው ይሆናል። የተቀሩት ደግሞ ሦስቱንም ትርጉም ሊይዙ ይችላሉ። ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ከቃል በቃል ትርጉም ሊፐጹ ስለሚችሉ በቀጥተኛ ትርጉሙ ላይ ሙጭጭ ማለት ብዙም አይጠቅምም።

እነዚህም ምዕራፎች በፍርሃትና በሥጋት ሳይሆን በማስተዋል እንድንመረምራቸው ሦስት ነገሮችን እንገንዘብ፡-

1. ይህ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑንና ስናጠናውም እግዚአብሔር ራሱን በውስጥ እንደሚገልጥልን ማመን፥
2. ለዘካርያስ ዘመን ሕዝብ እግዚአብሔር ራሱን ገልጦበታል። ስለዚህ ምንም እንኳ አንዳንድ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ግልጽ ባይሆኑም ተራ ሰዎችም ሊረዱት ይችላሉ፥
3. ምዕ. 9-14 ን ታሪካዊ ብቻ አድርገን መመከትና አንዳንድ ያለፉና የወደፊት ድርጊቶችን ዝርዝር ሁኔታዎች መተርጎም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን መልእክት መሳት ይሆናል። የወደፊቱን ሁኔታ ዝርዝር ለተገቢው ወቅት በእግዚአብሔር እጅ አንተወው።

ማብራሪያ

9፡1-8 ነፃነት ማለት ጠላቶችን ፀጥ ማሰኘት ማለት ነው። በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱት ጠላቶች የዘካርያስን ትንቢት ያዳምጡ ለነበሩት ሰዎች የወቅቱ ጠላቶች ነበሩ፥ በመጽሐፉ ውስጥ ከተጠቀሱት ፍፃሜ ያገኙ ትንቢቶች መካከል አንዱ ይህ ነው። ነቢዩ በቁ. 1-2 ውስጥ አልፎ አልፎ ሶሪያውያን የተሰኙትን የአራማውያንን የጦር ኃይል ይጠቁማል። ቀጥሎ የገንዘብና የንግድ ኃያላን የነበሩት ፊንቄያውያንን ይጠቅሳል፥ ቁ. 3-4። ታላላቅ የንግድ ወደቦች የነበሩት ጢሮስና ሲዶና ይዋረዳሉ። ከነዓን ከገቡበት ወቅት አንስቶ አይሁድን ሲያስጨንቁ የነበሩት አምስት የፍልስጥኤም ከተሞች በመጨረሻ ላይ ድል ይደረጋሉ፥ ቁ. 5-6። ከዚህ ወዲያ ግንም የባዕድ ኃይል የእግዚአብሔር ሕዝብ አያስፈራም፥ ድልም አያደርግም። የነርሱ መሸነፍ ቀና ውጤቶችን ያስገኛል፥ ይኸውም እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ይመልሳቸዋል፥ ቁ. 7-8።

እንዲሁም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ዕውነተኛ ነፃነት ልናገኝ የምንችለው ክርስትና ሕይወታችንን የሚዋጉትን የሰይጣን ጭፍሮች እግዚአብሔር ድል እንዲያደርጋቸው ስንፈቅድለት ነው።

9፡9-10 ነፃነት ማለት በእግዚአብሔር የተሾመው መሪ ወሰን የሌለው ሥልጣኑን እንዲያገኝ መፍቀድ ማለት ነው። የባዕድ ኃይሎች ብርታታቸውን የሚያሳዩት በፈረሶቻቸውና በወታደራዊ ጥንካሬያቸው ነው። መሪያቸው በጭራሽ የፋርስ መሪዎችን

ባይመስልም እንኳ መደሰት ነበረባቸው፥ ማቴ. 21፤5 ና ዮሐ. 12፡15። ቀድሞም ሆነ ወደፊትም አመጣጡ የተለየ ቢሆንም እንኳ «በልብህና በሕይወትህ ውስጥ መሪ ልሁን» እያለ እያንዳንዱን አማኝ መጠጋቱን ይቀጥላል።

የክርስቶስ አመጣጥ ያልታደለና ግርግር ያልበዛበት ቢሆንም ውጊያ ሁሉ የሚያስቆምና ዘላቂ ሰላም ማስገኘት እስኪችል የተሳካ ይሆናል። ቁ. 10 መንፈሳዊና ትንቢታዊ ፍፃሜ አለው።

9፡11-17 ነፃነት ማለት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች መውረስ ማለት ነው። በዚህ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሦስት የተለያዩ የተስፋ ቃሎች ተሰጥተዋል፥ ይህም ምናልባት በፋርስ ይኖሩ ለነበሩት ሊሆን ይችላል። እዚያ ከነበረው ምቾት የተነሳ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማስተዋልና ወደ ኢየሩሣሌም ለመመለስ ዝንባሌ አልነበራቸውም።

1. እርሱ ከእስራታቸው ይፈታቸዋል፥ ቁ. 11-13። በራሳቸው ብርታት ፋርስን ለቀው መውጣት አችሉም፥ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያዘጋጅላቸዋል። ከዚያም የበለጠውን ዕቁዱን እንዲፈጽሙ ይጠቀምባቸዋል።
2. እርሱ ይጠብቃቸዋል፥ ቁ. 14-15። በሚመለሱበት ወቅት ምንም ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይጠብቃቸዋል። በሚገጥማቸው ውጊያ ሁሉ ላይ ድል አድራጊ ይሆናሉ። ቁ. 15 የሚቀዳጁት የመጨረሻ ድል ምሳሌ መሆኑ ግልጽ ነው።
3. እርሱ ያድናቸዋል፥ ቁ.16-17። ይህ ደኅንነት ጥበቃንም ያጠቃልላል። የራሱ ሊያደርጋቸው ስለወሰነ ሐብቱ ሆነው ከእርሱ ጋር ይኖራሉ።

እነዚህ የተስፋ ቃሎች የእግዚአብሔርን አቋም በማንፀባረቃቸው ሌሎች ብዙ ትርጉሞች ይኖሯቸዋል። ለዘካርያስ ዘመን ነዋሪዎች የተሰጡ ነበሩ፥ የኛም ደግሞ ናቸው።

ማጠቃለያ

እሥራኤልን ያደናቀፏትና ድል ያደረጓት አራሚ ጎረቤቶችዋ ሁሉም ይሸነፋሉ። ሕዝቡ ይታገሉለት የነበረው ድል የእግዚአብሔር ስጦታ ይሆናል። በማንኛውም ዓይነት መንገድ ብርቱ መስለው ቢታዩም ድል ይደረጋሉ። ይህም እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ጌታ መሆኑን ይመሠክራል።

እግዚአብሔር ካልመራ ምንም ሰላም ሊኖር አይችልም። አንዳንድ ጊዜ የእርሱ አመራር ሰላም ሊያስገኝ የሚችል ያህል ኃይለኛ መስሎ ላይታይ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ሕዝቡ ራሳቸውን ለማስገዛት ፈቃደኛ እስካልሆኑ ድረስ እግዚአብሔር «የሰላምን ልዑል» ሊልክላቸው አይችልም።

ነፃነትና ራስን ማስገዛት አዲስና ያማረ አኗኗር ያስገኛል። የይሁዳው ኑሮ በፋርስ ሞልቃቃ ኑሮ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች እጅግ አይስባቸውም። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች የማትስበዋን ሥፍራ እጅግ አስፈላጊ ወደ መሆን ለውጧታል። ሕይወት ማለት እግዚአብሔር በሚሰጠው ነገር መርካት ማለት ነው።

ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

ጠላቶቻችን አሁንም ስለሚያሸንፉን ነፃነት ጎድሎናል? በማር. 7፡21-23 የተጠቀሱትን አንዳንድ የክርስቲያን ዋነኛ ጠላቶች ተመልከቷቸው። በእርግጥ አሁንም እኛን በመዋጋት ላይ መሆናቸው ጥርጥር የለውም፥ ይሁንና እነዚህ ነገሮች በሕይወታችን ውስጥ የሚመሩበት ትንሽ እንኳ ክፍት ሥፍራ አግኝተዋል? ወይስ የሕይወታችን ግዛት ሁሉ የእግዚአብሔር ነው? አንዳንድ ከባድ ውጊያዎች ሊያጋጥሙን ቢችሉም እንኳ ለመሸነፋችን ምንም ሰበብ ልንፈጥር አንችልም።

የሰላሙ ልዑል ወደ ሕይወታችን ሲገባና በቁ. 11 ውስጥ ያለውን ተስፋ የሚመስል ነፃነት ስንቀበል የሕይወታችንም ምልክት ደስታ ይሆናል። ያንን ነፃነት ካላገኘን ምን ይፈጸማል? ወደ ኢየሩሣሌም ገብቶ ሁሉን ፀጥ እንዳሰኘ ዛሬ ደግሞ እንደገና ንጉሣችን መሆኑን በዚች ቅጽበት ሊያረጋግጥ ይፈልጋል።

የእግዚአብሔር ነፃነት፤ ጥበቃና እንክብካቤ ዛሬም እንድንደሰትባቸው ተሰጥተውናል። «በፋርስ» መኖር የሚፈልጉት ሰዎች በነዚህ ነገሮች ሊደሰቱ አይችሉም። እነዚህ ሦስት ተስፋዎች ከመታዘዝ ጋር የተቆራኙ ናቸው፥ እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ልትጠቀሙባቸው ከፈለጋችሁ በትክክለኛው ሥፍራ ላይ መገኘት አለባችሁ። ከ «ፋርስ» ወጥታችሁ እነዚህን ነገሮች የራሳችሁ አድርጋችሁ ስትወስዷቸው ምን ለውጥ እንዳለው ትገነዘባላችሁ።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. በዘካርያስ ዘመን የአራም ዋና ከተማ ማን ነገረች? ቁ. 1
2. በኃብቷ የታወቀችው ከተማ ማን ናት? ቁ. 2-4
3. አምስቱን የፍልስጥኤም ከተሞች መጥቀስ ትችላላችሁ? ቁ. 5-7
4. የአቃሮን ሕዝብ ምን ይደርስበታል? ቁ. 8
5. የደስታ ጩኸት የሚጮኹት እነማን ናቸው? ለምን? ቁ. 9-10
6. ንጉሡ የሚመጣው እንዴት ነው? ቁ. 9-10
7. ሕዝቡን ነፃ የሚያወጣቸው ለምንድነው? ቁ. 11-13
8. በመጨረሻ ላይ ድል የሚጎናፀፈው ማን ነው? ቁ. 11-13
9. ሕዝቡን የሚጠብቃቸው ማን ነው? ቁ. 14-15
10. «በዚያ ቀን» ምን ይደረጋል? ቁ. 16-17

የውይይት ጥያቄዎች

1. በእግዚአብሔር የሚሸነፈው ማን ነው?
2. የእግዚአብሔር ድል ከሌሎች ድሎች የሚለየው እንዴት ነው?

3. ሕዝቡ ነፃ ሲወጡ ምን ያደርጋሉ?

4. የእግዚአብሔር ጥበቃ ውጤት ምንድነው?

5. ደኅንነቱ ምን ያደርጋል?

የቤት ሥራ

1. ብዙ ጊዜ በመደጋገም ምዕራፍ 9 ን አንብቡ። ይህ ምዕራፍ መወያያ ጊዜ የማናገኝላቸው ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች አቅፏል። ከምዕ. 9 የምትማሩትን ትምህርት ሁሉ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉት።

2. የምዕ. 10 አቢይ ትምህርት የእግዚአብሔር ማዳን ነው። ምዕራፉን ከቁ. 1-5፤ 6-7 ና 8-12 አድርጋችሁ በሦስት ክፍሎች በመክፈል ለሚቀጥለው ትምህርት ዝግጅት ለማድረግ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ አንብቡት።

ጥናት አሥራ አንድ - ምዕራፍ አሥር

የእግዚአብሔር ማዳን

ሕዝቡ እርሱን እንዳያገለግሉ ከሚያግዳቸው ማናቸውም ማገጃ ነፃ እንዲወጡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ይሁንና ይህ ሊሳካ የሚችለው ሕዝቡ ዕለት በዕለት በኃጢአት ከተበከለው ዓለም ማዳኑን ሲለማመዱ ነው። ስለዚህ ሁለት ዓይነት ማዳን አለ ማለት ነው። ይኸውም፡- ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውጭ ላሉት የሚሰጥና በውስጥ ላሉት የሚያገለግል ነው።

ይህ ደኅንነት የተቀባዩን ሰው ሕይወት ሁለንተና ይነካል። የእግዚአብሔር ልጆች አውቀውና ሳይውቁም በችግር ተወሳስበው ይገኛሉ። በችግር ውስጥ ተወሳስበው ሳሉ በእግዚአብሔር ሊደሰቱ ወይም ሊያገለግሉት አይችሉም። ምንም ነገር ሊያደርጉ ከመቻላቸው በፊት ከታሠሩበት የባርነት ቀንበር ፍፁም መላቀቅ አለባቸው።

አንዳንዴ ክርስቲያኖች ያሰሩአቸውን ነገሮች ሲመለከቱ ፈጽሞ የማይለወጡ ናቸው በማለት ይሠጋሉ። እግዚአብሔር ሊለውጠው የማይችለው ነገር በጭራሽ እንደሌለ ይህ ምዕራፍ ያሳስበናል። በምንም ነገር፤ በማንኛውም ወቅትና በየትም ሥፍራ ባሪያ መሆን የለብንም።

መሠረታዊ ነጥቦች

በባቢሎንና በኋላም በፋርስ ተወልደው ያደጉት ሰዎች ወደ ይሁዳ መመለስ የማይፈልጉበት በርካታ መልካም ምክንያቶች ነበሩአቸው። በዚህ ዘመን «የተበተኑት አይሁድ» የተሰኘው መጠሪያ ሐረግ የተከበረ አጠራር ሳይሆን አይቀርም። በይሁዳ ሊያመልኩና እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ የሚችሉትን ያህል በፋርስም የሚችሉ መስሏቸዋል። ሕዝቡ እንዲመለሱ እግዚአብሔር ያደረጋቸው ጥረቶች የሉም። ይህ የእነርሱ ምርጫ ነው።

መሢሑ ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ብዙ የሚፈጽግቸው ነገሮች አሉት። ሕዝቡ በፋርስ ወደ ይሁዳ እንዲመለሱ የእርሱ ፈቃድ ነበር። በ722 ዓከልበ በአሦርና በ586 ዓከልበ በባቢሎን በትኗቸዋል። አሁን እነዚህ ወቅቶች ተቀይረዋል። ሕዝቡ ከባቢሎን ምርኮ መማር የሚገባውን ነገር ሁሉ ተምሯል።

ብዙዎቹ ምርኮኞች በ536 ዓከልበ ተመልሰዋል። በተጨማሪ ሌላ ትልቅ ቡድን በ457 ዓከልበ ከእዝራ ጋር ሲመለስ በ444 ዓከልበ ደግሞ ሌሎች ሰዎች ከነህምያ ጋር ተመልሰዋል። ምናልባት ሌሎች ቡድኖች በተለያዩ ወቅቶች ሳይመለሱ አልቀሩም። ይሁን እንጂ ዘካርያስ በምዕ. 10 ላይ የሚያተኩረው እስከዚያ ወቅት በፋርስ በነበሩት ሰዎች ላይ ነው፥ ይኸውም «ወደ አገራቸው ለመመለስ» በጭራሽ ባልተደሰቱት ሰዎች ላይ ነው።

ማብራሪያ

10:1-5 ሕዝቡ በሕይወታቸው ውስጥ ቀዳሚውን ሥፍራ ለእግዚአብሔር ባለመስጠታቸው መንገዳቸውን ስተው ነበር። ወዲያው የማይረቡ ነገሮችን መሥራት ጀምረዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ዝናብ ለማግኘት ጣዖታትንና ሟርተኞችን እንዴት ይጠይቃሉ? ቁ. 1-2። እግዚአብሔር ብቻ ፈጣሪ መሆኑን ያውቃሉ። ይህም አጓጉል ድርጊት መንፈሳዊ ሁኔታቸው ምን እንደሚመስል ያሳየናል። ይሁን እንጂ በዛሬውም ዘመን አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች ጣዖታቸው ስሙን ቀይሮ «ገንዘብ» ይባል እንጂ ከእነርሱ የማይተናነሱ አጓጉል ነገሮችን ያደርጋሉ።

እግዚአብሔር ሕዝቡን አልረሳቸውም። የጨቆኗቸው ሁሉ ድል ይደረጋሉ። እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ቁጥጥር ሥር ነፃ ያወጣቸዋል። ወደታች ተጥሉ በመረገጥና በመሸነፍ ፈንታ ድል አድራጊ ይሆናሉ። ጠላቶቻቸውን ድል ያደርጋሉ፥ ቁ. 3-5። ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጎን ስለቆመ ነው። ማዳን ብቻ ሳይሆን ተሸናፊ የነበሩት አሸናፊዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

10:6-7 እነዚህ ጥቅሶች በፋርስ ለቀሩት ሰዎች የተነገሩ ሳይሆኑ አይቀሩም። እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ ምክንያትና በህይወታቸው ውስጥ የሚያስከትለው ውጤት በቁ. 6 ውስጥ ተሰጥቷል። ሕዝቡ ይህንን ማዳን ሲቀበሉ ፍፁም ይለወጣሉ። የአኗኗራቸውም ሁኔታ በሕይወታቸው ውስጥ የተፈፀመው ነገር የመለኮት ሥራ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

10:8-12 እግዚአብሔር ሕዝቡን የበተናቸው በኃጢአታቸው ምክንያት ነበር። ከርሱ እጅ ቅጣት ቀምሰዋል። አሁን አራት የተለያዩ ነገሮችን ሊያደርግላቸው ነው፥ ቁ. 8። ቁ. 9 የቁ. 8 ን ሃሳቦች በተጨማሪ ያስፋፋዋል። ይህ ማዳን የመለኮት ሥራ ነው። ሕዝቡ በራሳቸው ኃይል ሊድኑ አይችሉም። በቁ. 6፤ 7 ና 12 ውስጥ ብርታት የሚለው ወይም የእርሱ ተመሳሳይ ቃል አገልግሎት መስጠቱን አስተውል። ማዳኑ ለዳኑት ሰዎች ብርታት ሊያስገኝላቸው ነው።

ቁ. 10 ና 11 ከሞላ ጎደል ሥዕላዊ እንዲሆኑ የታቀዱ መሆናቸው ግልጽ ስለሆነ አላፊም ሆነ ትንቢታዊ አተረጓጎም ልንፈልግላቸው መፍጨርጨር አያስፈልገንም። በዚህ ዘመን አሦር ገና ግብፅ በመሸሽ ሊያመልጡ የሞከሩት ምርኮኞች የመጨረሻው ቡድን ሰዎች ናቸው፥ ኤር. 43-44። የተወሰዱት በቅድሚያም ይሁን በመጨረሻ እግዚአብሔር ያድናቸዋል። ወደ አሦር የተወሰዱት ቀዳሚዎቹ ናቸው። ገለዓድና ሊባኖስ የሚገኙት በሩቅ ሰሜን ነበር፥ ይኸውም ሊባኖስ በሰሜን ምዕራብ ስትሆን ገለዓድ በሰሜን ምስራቅ ትገኝ ነበር። በወራሪዎች ጥቃት የደረሰባቸው የመጀመሪያ አካባቢዎች እነርሱ ነበሩ፥ አሁን ግን ምንም የሚያስፈራቸው ነገር የለም። አሦርና ግብፅ ከ «ጭንቅ ባሕር»፤ ከ «ምገድና» ከጥልቀት ጋር ተያይዘዋል። እነዚህ ኃያላን መንግሥታት ማናቸውም ቢሆኑ እግዚአብሔር ተግባራዊ ሊያደርገው ያቀደውን ማዳን ማስቀረት የሚያስችል ምንም ኃይል የላቸውም።

እግዚአብሔር ካዳነ በኋላ ብርታት ይሰጣል፥ ከዚያም ሕዝቡ ብአምልኮና በመታዘዝ ምላሽ ይሰጣል፤ ቁ. 12።

ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ «ከመንፈሳዊ ፋርስ» ነፃ መውጣት ለሚያስፈልጋቸው የእግዚአብሔር ሰዎች የተፃፈ ነው። ሕዝቡ ከነበሩበት ሁኔታ ሳይላቀቁ ባሉበት ሁኔታ እግዚአብሔር ይመለከታቸዋል፥ ቁ. 2። ይህንን ያህል በግይረባ ስህተት ላይ ወድቀው ይቅበዘበዛሉ ግለት የግይታመን ይመስላል። ሆናም ግን ተረስተው አይቀሩም። በዚህ ሁኔታ መኖር እንደግይቀጥሉ እግዚአብሔር ያውቃል፥ ቁ. 5። ይህን ከመሰለው ባርነት ሊያድናቸው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፥ ቁ. 1።

የእግዚአብሔርን ግዳን ሊቀበሉ ፈቃደኛ ሲሆኑ ሁለት ነገሮችን ግድረግ እንዲችሉ ያበረታቸዋል። ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚችሉበትን ብርታት ያገኛሉ። እርሱን ግገልገል የሚያስችልም አቅም ይኖራቸዋል። ይሁንና ይህንን ብርታት ሊያገኙ የሚችሉት ከፋርስ ሲወጡ ብቻ ነው።

ሕዝቡን ከፋርስ መልሶ ግምጣትና ግዳን እንዲሁም በተሰፋይቱ አገር እንዲደሰቱ ግድረግ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። የእግዚአብሔር ግዳን ምድራዊና ሰግያዊም ነው። ዕብ. 4 ባጠቃላይ የሚናገረው ስለዚህ ዕረፍት ነው። ይህም እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደሚቆጣጠር የግወቅ ግረጋጫ ነው። የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል «በግብፅ» ወይም «በአሦር» በየትም ሥፍራ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ሊያድነው ይፈልጋል።

ከሕይወት ጋር የሚዘመዱ ነጥቦች

በውስጣችን የተዘራው ዘር ፍሬ እንዲያፈራና በጥልቀት ሥር እንዲሰድ እግዚአብሔር በልቦቻችን ውስጥ ዝናቡን እንዲያዘንብ እንጠይቀው። የእግዚአብሔርም ዝናብ ልቦቻችንን ሲያረሰርስ ምሪት አግኝተን ሕይወታችን ትርጉም የሚሰጥና ዓላማ ያለው ይሆናል፥ ፋርስን ትተን መውጣትም እንችላለን።

አብዛኛውን ጊዜ ግብና ፍፃሜው ጨርሶ ሊገናኙ የግይችሉ መስሎ ይታየናል። እግዚአብሔር የሚጠብቅብንና ልናገኘው እንችላለን ብለን የምናስበው ነገር የግይገናኙና የጋራ የሆነ ነገር የሌላቸው ይመስላሉ። እግዚአብሔር ብርታት ካልሰጠ ይህ በእርግጥም እውነት ነው። እግዚአብሔር ብርታት የሚሰጠን ደካማነታችንን በምንረዳበት ወቅት ነው።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የዕረፍት ሥፍራ ሲያዘጋጅላቸው ለምን ይቅበዘበዛሉ? ሕዝቡ ከኃጢአታቸው የተነሳ ከአሦር እስከ ግብፅ ድረስ ተበትነው ነበር፥ እግዚአብሔር ግን እንደገና ሰብስቦ ሊያመጣቸው ይፈልጋል። ሕዝቡም ሊመለሱ ፈቃደኛ ሲሆኑ ምንም ባሕር ወይም ወንዝ ሊያገዳቸው አይችልም። ዛሬውኑ ይህንን ተግባራዊ እናድርግ።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ዝናብን የሚሰጠው ማን ነው? ቁ. 1
2. ሕዝቡ ከሥፍራ ሥፍራ ለምን ተቅበዘበዙ? ቁ. 2
3. በዚህ ወቅት እግዚአብሔር የሚቀጣው ማንን ነው? ለምን? ቁ. 3
4. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ያደርግላቸዋል? ቁ. 5
5. የሚያድናቸውስ ለምንድነው? ቁ. 6
6. የሚያደርጉት ነገር ምንድነው? ቁ. 7
7. በአንድነት ሲሰበሰቡ ቁጥራቸው ስንት ይሆናል? ቁ. 8
8. ወደ ይሁዳ የሚመለሰው ማን ነው? ቁ. 9
9. የሚኖሩት የት ነው? ቁ. 10
10. እርሱስ የሚረዳቸው እንዴት ነው? ቁ. 11-12

የውይይት ጥያቄዎች

1. እሥራኤልና ይሁዳ እግዚአብሔርን ሲረሱ ምን ደረሰባቸው?
2. እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያበረታው ለምንድነው?
3. እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው ብርታት ምን ዓይነት ነው? ቁ. 6-7
4. እስካሁን ተበትነው ለሚገኙት የሚደርሳቸው ጥሪ ምን የሚል ነው?
5. ቁ. 10-12 ምን መንፈሳዊ ትርጉም ይኖረዋል?

የቤት ሥራ

ምዕ. 10 ን ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ ማንበብ አትርሱ። አስፈላጊ ሆኖ ካገኛችሁት ከማስታወሻ ደብተራችሁ ጋር አገናዝቡት። ምናልባት ክፍለ ምንባቡን ለመገንዘብ እንዲረዳችሁ የራሳችሁ የሆነ ማስታወሻ ውሰዱ።

ምዕ. 11 የሰብዓዊ አመራርን ደካማነት ሲያመለክተን እግዚአብሔር ሁሉን በቁጥጥሩ ሥር ማድረጉንም ደግሞ ይጠቁመናል። ይህ ምዕራፍ ለየት ያለ መስሎ ቢታይም እንኳ ለሚቀጥለው ጥናት ዝግጅት ለማድረግ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ መላልሳችሁ አንብቡት።

ጥናት አሥራ ሁለት - ምዕራፍ አሥራ አንድ

አንክብካቤ

ጌታ ስለሚጠነቀቅላቸው ክርስቲያኖች ሸክማቸውን በእርሱ ላይ እንዲጥሉ ጴጥሮስ ነግሮአቸዋል፥ 1ኛ ጴጥ. 5፡7። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለሚጠብቁት እረኞች ነቢዩ ኤርምያስ በምዕ. 23፡2 ላይ ይናገራል። ለመንጋው እንክብካቤ በሚያደርጉትና በመንጋው በራሱ መካከል አንዳንድ የመመሳሰል ነገር ይታያል። ግዴለሽ መንጋ የሚያጋጥመው ግዴለሽ እረኛ ነው። መንጋውም እረኛውም ለምንም ነገር ግድ የላቸውም።

ይሁንና መንጋውና እረኛው በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ሥር ሲሆኑ እርስ በርስ ይተሳሰባሉ። በምዕ. 11 ውስጥ መንጋውም ሆነ እረኞቹ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቃልና ለውጤቶቹ ለማስገዛት ፈቃደኛ አልነበሩም። ራሳቸውን ለቃሉ ስለማያስገዙ እርስ በርስ አንዱ ለሌላው ራሱን አያስገዛም። እርስ በርስ አንክብካቤ መደራረግ ባለመውደዳቸው እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ነገር አንቀበልም ብለዋል።

ልክ ለእሥራኤላውያን ድርጭት እንደሰጣቸው እግዚአብሔር ለእረኞቹ ለመንጎቹም የሚፈልጉትን ሁሉ ሰጥቷቸዋል። ከዚያ የተሻለ ነገር እናገኛለን ብለው በማሰብ እግዚአብሔር ሊያደርግላቸው የሚፈልገውን እንክብካቤ አንፈልግም ብለዋል። ስለዚህ ከሁሉም ሳይሆኑ ቀርተዋል። እርስ በርስ አንዱ ለሌላው እንክብካቤ እንደማያደርግና ማንም እንደማይንከባከባቸው ተመልክተዋል።

መሠረታዊ ነጥቦች

አንድ ምሁር፡- ዘካ. 11 ን «እጅግ በጣም እንቆቅልሽ የሆነ የብሉይ ኪዳን ትንቢት» ብሎ ጠርቶታል። ይህም ትንቢቱን ወይም ምሳሌውን ለመተርጎም በምናደርገው መፍጨርጨር ላይ የተደገፈ ሊሆን ይችላል። ምናልባት አንዳንድ ተርጓሚዎች በምዕራፉ ውስጥ ጨርሶ የማይገኝ መረጃ ከራሱ ከምዕራፉ ለማግኘት ጥረት ያደርጉ ይሆናል።

ዝርዝር ሁኔታው ግልጽ እንዳይሆን ስለተፈለገ የተብራራ አይደለም ማለት ነገሩን ከሚገባ በላይ ማቃለል ይሆናል። ነቢዩ በአእምሮው ውስጥ ምንም ዓይነት የተወሰነ ሁኔታ ላይዝ ይችላል። ምሳሌው ወይም ትንቢቱ በግብር የተፈጸመ ነገር ከሆነ ፍፃሜ ያገኘው ኢየሩሣሌም ውስጥ ነው።

ምናልባት ይህ ትንቢት ወይም ምሳሌ የተነገረው በፋርስ ለሚገኙ አንዳንድ መሪዎች ሊሆን ይችላል። የክፍሉ ቋንቋ ግልጽ ያልሆነውም ለዚህ ይሆናል። ብዙ የማብራሪያ መጻሕፍት በመቃባውያን ዘመን የተፈጸመ ድርጊት አምጥተው ሊያያይዙ ሞክረዋል፥ ይህንን ግድረግ ምንም ጥቅም ያለው መስሎ አይታይም። ይህንን የሚያደርጉ አብዛኛዎቹ ምሁራን ምዕራፉ የተፃፈው በዚያ ዘመን ነበር ሲሉ የተሳሳተ ግምት ይሰነዝራሉ። የነቢዩ ዘካርያስን ዘመን ከመጠቆም ሌላ ምንም ሐሳብ ከምዕራፉ ማግኘት አይቻልም።

ምናልባት ይህ ትንቢት ወይም ምሳሌ የተነገረው በፋርስ ለሚገኙ አንዳንድ መሪዎች ሊሆን ይችላል። የክፍሉ ቋንቋ ግልጽ ያልሆነውም ለዚህ ይሆናል። ብዙ የግብራሪያ መጻሕፍት በመቃባውያን ዘመን የተፈጸመ ድርጊት አምጥተው ሊያያይዙ ሞክረዋል፥ ይህንን ግድረግ ምንም ጥቅም ያለው መስሎ አይታይም። ይህንን የሚያደርጉ አብዛኛዎቹ ምሁራን ምዕራፉ የተፃፈው በዚያ ዘመን ነበር ሲሉ የተሳሳተ ግምት ይሰነዝራሉ። የነቢዩ ዘካርያስን ዘመን ከመጠቆም ሌላ ምንም ሐሳብ ከምዕራፉ ግግኘት አይቻልም።

ከእሥራኤልና ከይሁዳ ታሪክ ይህንን የመሰለ የእረኞችና የበጎችን ባሕርይ የሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎችን መሰብሰብ ይቻላል። ሕዝቡ አዘውትረው የእግዚአብሔርን ጥበቃ እምቢ ብለዋል። አጠቃላይ አቢይ ትምህርቱ በምንም መንገድ የተለየ ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔርን አመራር የመቃወም መጨረሻ ሁከትና መለያየት ነው። ምናልባትም የምዕራፉ አቢይ ትምህርት ይህ ሳይሆን አይቀርም።

ማብራሪያ

11፡1-3 እነዚህ ሦስት ጥቅሶች ትንቢቱን በሚመለከት በግጥም መልክ መግቢያ ይሰጡናል። ግጥሙ ከሊባኖስ ተራሮች በመነሳት በስተምዕራብ በኩል ይጓዝና ኮረብታማውን አገር ባሳንን አቋርጦ በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ አድርጎ ዮርዳኖስ ሸለቆ ላይ ያቆማል፥ ይኸውም ከተራራው ሰንሰለት እስከ ሸለቆው ግለት ነው። ዛፎቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ተገልፀዋል፥ ይኸውም ከሊባኖስ የዝግባ ደን እስከ ዮርዳኖስ ሸለቆ ቁጥቋጦ ድረስ ያሉት ተገልጸዋል። ሁሉም ይጠፋሉ። በቁ. 3 ላይ መሪዎች በሙሉ በተለይም በምዕ. 10 የተጠቀሱት የግብፅና የአሦር መሪዎች መጠለያ ባጡ አንበሶች ተመስለዋል።

11፡4-6 ነቢዩ በድርጊት የታየ ምሳሌ ያቀርባል። በጎቹና እረኞቹ ዕድላቸው ጥፋት ነው። ለመንጋው እንክብካቤ ማድረግ የነበረባቸው እረኞች የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ያሳድዳሉ። በጎቹ መልካምን እረኛ አንፈልግም ብለውታል፥ ስለዚህ በጨካኝ እረኞች እጅ ይወድቃሉ።

11፡7-14 ምሳሌው በጎቹንና እረኞቹን እንዲናገር ታቅዶ የቀረበ ነው። ነቢዩ የመለኮታዊ ፀጋ ልዩ ምልክት ሆኖ በሕዝቡ መካከል ተልኳል፥ ሕዝቡን ለማዳን የእግዚአብሔር መጠቀሚያ ሊሆን ይችል ነበር። በሕዝ. 37፡15-23 ና በሌሎች ቦታዎች እንደምንመለከተው ሁለቱ በትሮች የሚጠቁሙት የሰሜኑንና የደቡቡን መንግሥታት ቢሆንም እንኳ ቁ. 7 ላይ ምናልባት ሁኔታውን ማየት በሚቻል መንገድ ለመግለጽ ሊባል ብቻ በአገልግሎት ላይ የዋሉ ሳይሆኑ አይቀሩም። እግዚአብሔር የሾመው እረኛ ለመንጋው እንክብካቤ በሚያደርግበት ወቅት የሥራው መለያ «ፀጋ» ና «አንድነት» ናቸው።

ለመንጋው የሚያደርገው ጥበቃ በቁ. 5 ላይ የተጠቀሱትን ያስወግዳል፥ ቁ. 8 ን ተመልከቱ። ዘካርያስ በአእምሮው ውስጥ ያሰባቸው ሦስቱ ሰዎች እነ እገሌ ናቸው ብሎ ግምት መሠንዘር በእውነቱ ተገቢ አይደለም። መንጋው አሁንም ምንም አያስተውልም።

ከዚያም መልካሙ እረኛ ያንኑ ነጥብ ለማጉላት ይኸውም መንጋው የእግዚአብሔርን እረኛ ባይቀበሉ እንደሚበተኑ ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ሁለት ነገሮችን አድርጓል።:-

1. እንዱን በትር ሰብሮታል፥ ቁ. 10።

2. ሥራውን በፈቃዱ ትቷል፥ ቁ. 12።

ነቢዩ የሦስቱ ክፍሎች ማለት የሦስቱ እረኞች መባረር፤ የእንዱ በትር መሰበርና የመልካሙ እረኛ ሥልጣኑ በፈቃዱ መተዉ ትርጉም ይመለከቱ ለነበሩት እረኞች በሙሉ ግልጽ እንደ ነበር ቁ. 11 ወረድ ብሎ ያረጋግጥልናል። በጎቹ የእግዚአብሔርን ፀጋ አንቀበልም እስካሉ እግዚአብሔር ምን ሊያደርግላቸው ይችላል?

ሁለት ተጨማሪ ምሳሌያዊ ድርጊቶች ቀጥለው ቀርበዋል:-

1. የገንዘቡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ መቀመጥ፥ ቁ. 13።

2. የሁለተኛው በትር መሰበር፥ ቁ. 14።

በዚህ ወቅት መልዕክቱ እንደ መስታወት ጥርት ያለ ነበር፥ ይኸውም መንጋውና ሌሎቹ እረኞች የእግዚአብሔር እንክብካቤ በተደጋጋሚ አንቀበልም ካሉ እነርሱን ከመተው በቀር ሌላ አማራጭ የለውም። ይህም መልዕክት ለሕዝቡ አዲስ አልነበረም፥ ሕዝ. 11:23 ና ማቴ. 23:28። ገንዘቡ ልክ በምዕ. 6:14 እንደተመለከትነው ዘውድ በቤተ መቅደስ ውስጥ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ምስክር እንዲሆን ነበር። ነቢዩ የተሰበሩትንም ሁለቱን በትሮች በቤተ መቅደስ ውስጥ ያስቀምጣቸዋል? ይህ ምናልባት ጳውሎስ በዕብ. 6:6 ላይ የተናገረው ዓይነት «የማይቻል» ሁኔታ ሊሆን ይችላል። በፀጋ ፈንታ ፍርድ፤ በአንድነት ፈንታ ደግሞ ሁከት ይሆናል።

11:15-17 በዚህ በሁለተኛ ደረጃ በቀረበው ምሳሌ ውስጥ ነቢዩ ምን እንዳደረገ አልተገለጸልንም። በቁ. 16 ላይ የተጠቀሰው «እረኛ» የሚለው ቃል አንድ የሚታወቅ እረኛን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ከሆነ ይህ እረኛ ማን እንደሆነ አናውቅም፥ በአተረጓጎም ላይም ለውጥ ሊያመጣም አይችልም። እረኛው የተሰጠውን አደራ በመፈጸም ፈንታ ኃላፊነት የማይሰማው ነበር፥ ለዚህ ተግባሩም ቅጣት ይቀበላል።

ማጠቃለያ

በግ የሚመስል ሁሉ የመንጋው አካል አይደለም! ማቴ. 7:21-23 ተመልከቱ። ነቢዩ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚናገረው ስለ አመፀኛ በጎች ነው። በንግግር ደረጃ እነዚህ በጎች የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ሲሆኑ በግብር ግን ራሳቸውን ከእግዚአብሔር በረከቶች ከልል ውጪ አድርገዋል፥ ምዕ. 11 የሚመለከተው በምዕ. 10 ውስጥ የቀረበውን ልመና አንሰማም ያሉትን ሰዎች ይሆናል። ምዕ. 11 የሚያወራው ስለ ሁለት ዓይነት እረኞች ብቻ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። መንጋው የእግዚአብሔርን የእንክብካቤና የአሳቢነት መጠይቅ አልቀበልም ስላለ እግዚአብሔርም ደግሞ ትቶታል።

ጥቅመቢስ ስለሆኑ እረኞች የሚቀርበው ጥያቄ ምንጊዜም አሰቸጋሪ ነው። እግዚአብሔር እነዚህን በመልካም እረኞች ለምን አይተካቸውም? የሚል ጥያቄ

በተለምዶ አንጠይቃለን። አንዱ ምክንያት እዚህ ክፍል ውስጥ ቀርቧል፥ ይኸውም በጎቹ ለሥራቸው ተገቢ የሆነውን ዋጋ አግኝተዋል የሚል ነው። የእግዚአብሔርን ጥበቃ አንቀበልም ሰላሉ እርሱ መልካም እረኞቹን አንስቶ የቅጣት መሣሪያዎቹ የሆኑትን ክፉ እረኞች በፈንታቸው አስቀምጧል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ «ጥቂቶቹ ታማኞች» ምንም ነገር አልተነገረንም። ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት ዘመን ውስጥ እግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የሚቆሙለትን ሰዎች ሊጠብቃቸው ይችላል። እረኞቹና አብዛኞቹ በጎች አመጸኞች ሊሆኑ ቢችሉም እንኳ መንጋውን ከመከተል ይልቅ ወደ እርሱ የሚመለከቱትን ሰዎች እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል።

ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

እግዚአብሔር መንጋውን ቸል አይልም ወይም አይተውም። ይሁን እንጂ በመንጋውና ከመንጋው ውጭ ባሉት መካከል የአቋም ልዩነት አለ። ኤርምያስ ለ40 ዓመታት የኢየሩሣሌምን ሰዎች እንዲማጠን እግዚአብሔር ልኮታል። የእግዚአብሔር ትዕግሥት የሚያልቅ አይደለም፥ ሆኖም ፍርድ እስኪመጣ ድረስ በመንጋው መመለስ ይደሰት ነበር፥ ሮሜ 10፡21።

እንደ ሳያል ያሉት እረኞች ዋጋ ቢስ ናቸው፥ ሊመጣ የሚችለውን ውጤት መገንዘብ አስተዋይነት ነው። ጢሞቴዎስ መሪዎችን ሲመርጥ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ጳውሎስ አስገንዝቦታል፥ እኛም ለመሪዎች እንድንፀልይ ተመክረናል። ሥልጣን በጨበጡባቸው የመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ በቂ ሥልጠና መስጠት ኃላፊነታቸውን እንዲገነዘቡት ያደርጋቸዋል። መንጋው ለእረኞቹ ግድ ከሌለው ለመንጋው የማያስቡ እረኞች ያጋጥሙታል።

ሁኔታው ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆን እግዚአብሔር አይፈቅድም። እርሱ የእረኞቹንና የመንጋውን ፍላጎት ያውቃል። እግዚአብሔር ፍርዱ ለዘለቄታው እንዲቆይ አያደርግም። ሆኖም ታማኞቹ በነዚህ ወቅቶች ውስጥ መልካሙ እረኛ በሚያደርግላቸው ጥበቃ ላይ ሊታመኑ ይችላሉ።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የዝግባ ዛፎቹ የሚገኙት የት ነበር? ቁ. 1
2. በባላን የሚገኘው ምን ዓይነት ዛፍ ነው? ቁ. 2
3. አንበሶቹ የሚያገሱት ለምንድነው? ቁ. 3
4. ዘካርያስ የተናገረው ለምን ዓይነት መንጋ ነበር? ቁ. 4
5. መንጋውን ይጠብቁ የነበሩት እረኞች ምን አደረጉ? ቁ. 5
6. በጎቹን የሚቀጣው ማን ነው? ቁ. 6

7. ነቢዩን የቀጠረው ማን ነው? ቁ. 7

8. ነቢዩ በዚህ ወቅት የተናገረውስ ለማን ነው? ቁ. 9

9. የነቢዩ ደመወዝ ምን ነበር?

10. በቁ. 15-17 ውስጥ ፍርድ የተላከው በማን ላይ ነው?

የውይይት ጥያቄዎች

1. የቁ. 1-3 ዓላማ ምንድነው?

2. ዘካርያስ እረኛ እንዲሆን የተነገረው ለምን ነበር?

3. የሁለቱ በትሮች ፍቺ ምንድነው?

4. ማቴ. 27፡9-10 ን ከማቴ. 11፡12-13 ጋር አወዳድሩ።

5. ዘኁ 11፡15-17 ከሕዝ. 34 ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

የቤት ሥራ

የምዕራፉን አጠቃላይ መልእክት በጥልቀ እስክትገነዘቡ ድረስ ምዕ. 11 ን ደጋግማችሁ ብዙ ጊዜ አንብቡት። በተሰጣችሁ ማብራሪያ ላይ ተጨማሪ አድርጋችሁ የራሳችሁን ማስታወሻ ውሰዱ።

ምዕ. 12 እግዚአብሔር እንዲያገለግሉት የሚፈልጋቸውን ሰዎች በሚመለከት ስላደረገው ምርጫ ይናገራል። ይህ ምዕራፍ ከቁ. 1-9 ና ቁ. 10-14 ሆኖ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። ለሚቀጥለው ጥናት ለመዘጋጀት ምዕራፉን አንብቡት።

ጥናት አሥራ ሦስት - ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ምርጫ

«የተመረጡ» ተብለው የተጠሩ ሰዎችን የሚያመለክቱ በርካታ ጥቅሶች እናገኛለን፥ ለምሳሌ፦ - ማቴ. 24፡22፥ ሉቃስ 18፡7፥ ሮሜ 8፡33 ና 11:7፥ ቲቶ 1፡1 ወዘተ። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር በዓለም ላይ በሚሠራው ሥራ ውስጥ ልዩ ዓላማ አላቸው። እግዚአብሔር ለእነርሱ ያዘጋጀው ልዩ ሥራ ስላለው ለደህንነታቸውም ደግሞ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

እንዲሁም ይህ ማለት እግዚአብሔር ዕቅድ አቅዶላቸዋል ማለት ብቻ ሳይሆን እርሱን ግገልገል እንዲችሉ በተወሰነ መንገድ እንዲኖሩ ይፈልጋል ማለት ነው። ሕዝቡ ምላሽ መስጠት ቢሳናቸው ለእነርሱ አቅዶት የነበረውን ነገር ለሌሎች ይሰጠዋል። ከዚህም ምክንያት የተነሳ ሁለት አሻሚ ሐሳቦች ያጋጥሙናል፦ 1. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ከመታዘዝ ጋር የተቆራኙ ናቸው፥ 2. የእግዚአብሔር ቃል በጭራሽ አይለወጥም።

እግዚአብሔር የሚያተኩረው በአንድ ግለሰብና በደህንነቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላ ቤተሰቡ ላይ ነው። ይህ ምዕራፍ የሚናገረው ስለ እሥራኤል ሲሆን ስለ ኢየሩሳሌምም ብዙ ነገሮች ያወራል። እግዚአብሔር ቅድሚያ የሚሰጠው ለምድሪቱ ወይም ለከተማይቱ ሳይሆን በነዚህ ሥፍራዎች ለሚኖረው ማሕበረሰብ ነው። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ዕቅዶችና ዓላማዎች ውስጥ ልዩ ሥፍራ ይዘዋል። ይህ ምዕራፍ ልዩ ትኩረት የሚያደርገው በእግዚአብሔር ቤተሰብ ደህንነት ላይ ነው።

መሠረታዊ ነጥቦች

ሕዝቡ በየጊዜው ለእግዚአብሔርና እርሱ ሊያደርግላቸው ለሚፈልገው ነገር ጀርባቸውን ሰጥተዋል፥ ዘካ. 10፡2፥ 11፡ 4 ና 7። ይህም ሆኖ እንኳ እግዚአብሔር አይረሳቸውም ወይም ቸል አይላቸውም። ባዕዳን ኢየሩሳሌምን ሲመለከቷት እግዚአብሔር የረሳትና ቸል ያላት ከተማ መስላ ሳትታያቸው አይቀርም። አስታውሱ! ቤተ መቅደሱ አገልግሎት መስጠት ቢጀምርም እንኳ ሕዝቡ ከተማይቱን ለማደስ ምንም ሥራ አልጀመሩም ነበር።

የከተማይቱ ውስጣዊ ድክመቶች ብዙ ነበሩ። አብዛኛው ሕዝቡ ከተማይቱን ትቶ በገጠር ሊኖር እንደሄደ ከሚልክያስና ከነህምያ እንረዳለን። ሞዓብንና ኤዶምን የመሳሰሉት የኢየሩሳሌም ጎረቤቶች ምድሪቱን ወርረው ለማጥፋት ዝግጁ ነበሩ። ከውጫዊ ሁኔታዋ አንፃር ሲታይ ከተማይቱ ተስፋ ያላት አትመስልም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «ኢየሩሳሌም» የሚለው ቃል በዚህ ስም የምትጠራዋን ከተማ ያመለክታል። ሆኖም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ባጠቃላይ ሊወክልም ደግሞ ይችላል። ስለዚህ ምዕራፉ ከአንዳንድ አንፃሮች ሲታይ ከኤፌሶን መልእክት ጋር ይመሳሰላል፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን እንደሚያደርግ ይነግረናል።

የእግዚአብሔር ቃል ጨርሶ አይለወጥም። ይሁን እንጂ ተቀባዮቹ ይለወጣሉ። ቃሉ የተነገራቸው ሰዎች ባይቀበሉት ለሌሎች ይሆናል። ለምሳሌ እግዚአብሔር በነነዌ ላይ እንደሚፈርድ ተናግሯል፡ ዮና. 3፡4 ና 10። መልእክቱ የደረሰው ትውልድ ንስሐ ስለገባ ፍርዱ ወዲያው ተግባራዊ አልሆነም። ከመታዘዝ ጋር የተቆራኙትን የኤር. 12፡14-17 ተስፋ ቃሎች ተመልከቷቸው። በቁ. 14-15 ላይ የተሰጡት የተስፋ ቃሎች ሲሆኑ በቁ. 16-17 በቅድሚያ መፈጸም ያለባቸው ነገሮች ተጨማሪ ሆነው ቀርበዋል። በግዑዙ ዓለም ላይ እንዲሠራባቸው ካወጣቸው የማይሻሩ ሕግጋት አኩል የእግዚአብሔር ቃልም የታመነ ነው፤ ኤር. 33፡23-26።

ማብራሪያ

12፡1-9 ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን የሚገባው ጌታ ፍጥረትን በሚመለከት በሦስት ዓይነት መንገድ ተገልጿል፤ እርሱ አሁንም ፈጣሪ ነው፤ በመዝ. 51፡10 ላይ « . . . ፍጠርልን» የሚል ልመና እናገኛለን። ይህ መልእክት በየትኛውም ዘመን ለሚኖር ሕዝቡ የተሰጠ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የእግዚአብሔር ሕዝብ የያዘውን ማዕከልና አካባቢውን የማጥፋት ሙከራ ያደርጋሉ። «ዓለም» እግዚአብሔር የገነባውን ለማፍረስ ብርቱ ጥረት ታደርጋለች፤ ኃጢአት ዘወትር ይህንን ያደርጋል። ይሁን እንጂ ምንም የጠላት መጠንና ብርታት ብዙ ቢሆን እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል፤ ያስታጥቃል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲድን ይህ የራሱ የጌታ ሥራ እንጂ የሰው አለመሆኑ በግልፅ ይታወቃል።

በቁ. 6 የተጠቆመው የውጊያ ወቅት ሕዝቡ በቡድንም ሆነ በተናጠል «ሰይጣንን በእግሩ ሥር ለመርገጥ» እግዚአብሔር ያስችለዋል። እግዚአብሔር በከተማይቱ ውስጥ ያሉትንና አንድ ወይም ሁለት ሆነው በይሁዳ የገጠር አካባቢዎች የተበተኑትን ሰዎች ይጠብቃቸዋል። በእርግጥ በገጠር የሚኖሩት ሰዎች ልዩ በረከት ይቀበላሉ፤ ቁ. 7። በእግዚአብሔር ሕዝብ ሕብረት መካከል መገኘት መባረክ ነው። ጥበቃ ይደረግላቸዋል፤ ብርታት ያገኛሉ፤ እንዲሁም የመምራት ችሎታ ይሰጣቸዋል። ከዚያም እግዚአብሔር አንድ ልዩ ነገር ያደርጋል። ይኸውም ጠላቶቻቸውን በማጥቃት ጨርሶ ያጠፋቸዋል። ሕዝቡም ወደፊት ሊገጥማቸው ከሚችል ጥቃት ይተርፋሉ። ውጊያው ጭራሽ የሚያቆም ዓይነት አይደለም፤ የሚያከትመውም በሽንፈት አይደለም።

12፡10-14 ቁ.6፤8 ና 11 «በዚያን ቀን» በማለት ይጀምራሉ። ነቢዩ የሚያመለክተው የትኛውን ቀን ነው? ምናልባት እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ለሚኖረው ሕዝቡ ከቸርነቱ የተነሳ ብርታት የሚሰጥበትን በቁ. 5 ላይ የተጠቀሰውን ቀን ይሆናል። በዚያ ወቅት እግዚአብሔር በጠላቶች ላይ ድል መስጠት ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ መንፈሳዊ ለውጦችንም ደግሞ ያስገኛል። በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁድና ሌሎቹም አሕዛብ፡-

ሀ/ መሐሪ ልብ ይኖራቸዋል፤ የእግዚአብሔርን ምሕረት ተቀብለው እነርሱም መሐሪ ይሆናሉ።

ለ/ የፀሎት መንፈስ ይኖራቸዋል፥ ከሚወዳቸውና ከሚንከባከባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሊዛመዱ ይናፍቃሉ።

በ11፡12 ውስጥ የተጠቀሰው «ዋጋዬን ስጡኝ» ና ወዘተ የእግዚአብሔርን የምሕረት መልእክተኛ መቃወማቸውን ያመለክታል፥ ዮሐ. 19፡37 ንና ራእ. 1፡7 ን አመሳክሩ። ንስሐቸው በለቅሷቸው መጠን ተገልጿል። ቁ. 11 ከነዓናውያን አምላካችን ሞቷል ብለው በማሰብ በሕብረት ሲጮሁና ሲላቀሱ የሚያሳይ የአራሚን ልማድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ 1ኛ ነገ. 18፡27-29ን ተመልከቱ።

እውነተኛው ንስሐ በግል የሚደረገው ነው፥ ቁ. 12-14። ዳዊት፤ ዳታን፤ ሌዊና ሰሜኢ ለምን እንደተጠቀሱ የሚገልጽ ጉልህ ምክንያት አይታይም። እያንዳንዱ ቤተሰብ ወንድና ሴት አንድም ሳይቀር ከልብ ንስሐ ይገባል። በምዕ. 12፡2-5 ውስጥ እንደተጠቀሰው ይህ የተሰጠው ለእግዚአብሔር የድልና ብርታት ስጦታዎች ተገቢ ምላሽ ተደርጎ ነው።

ይህ ምዕራፍ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር የተላከውን እረኛ አንቀበልም ካለበት ክፍል ከምዕ. 11 ጋር መያያዝ ያስፈልገዋል። በተጨማሪ ከምዕ. 13 ጋርም ደግሞ መያያዝ አለበት። ንሥሐ በምዕ. 13፡1 ላይ የተጠቀሰውን ምላሽ ያስገኛል።

ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ሕዝብ ብዙ ጊዜ ተሸንፏል። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ሽንፈት በኃጢአታቸው ምክንያት የመጣ የእግዚአብሔር ቅጣት ነው። የመጣባቸው በኃጢአታቸው ምክንያት ካልሆነ እግዚአብሔር የጠላቶቻቸውን ጥቃቶች ሊቋቋሙ የሚችሉበት <u>ብርታት ይሰጣቸዋል</u>፥ 12፡5 ና 8። ጠላቶቻቸው ሊያሸንፏቸው የሚችሉት እግዚአብሔር ሊፈቅድላቸው ብቻ ነው፥ 2ኛ ቆሮ. 11፡12-16፡10። የጠላቶች ወረራ ምንም በጭካኔ ቢሞላም የማታ ማታ ድሉ የእነርሱ አይደለም።

ከተለያዩ አቅጣጫዎችና በልዩ ልዩ ሕዝብ አማካይነት ጥቃቶች ሊመጡ ይችላሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ <u>እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል</u>፥ 12፡8። እግዚአብሔር ብርታት መስጠት ብቻ ሳይሆን ራሱ በውጊያው ውስጥ ሊሳተፍ በሥፍራው ይገኛል። እርሱ ሕዝቡን ለጠላቶቻቸው ጥቃት በጭራሽ አሳልፎ አይሰጣቸውም።

ይህንን የመሰለው ድል ሊያስከትል የሚችለው ትዕቢትን ብቻ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕግጋቱንም ደግሞ ይሰጣል። ሕዝቡም ጠቃሚ የሆነውንና የማይጠቅመውን ነገር ለይቶ ሊያውቅ ይችላል። እግዚአብሔር የሚሻውን ተስማሚ ምላሽ ለይተው ያውቃሉ። በመዋረድና በንስሐም ወደ እርሱ ይቀርባሉ።

ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

በምዕ. 12 ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊሰጥ የሚፈልጋቸው ቢያንስ ሦስት ነገሮች ይኖራሉ። እግዚአብሔር አልተለወጠም። የተስፋ ቃሎቹ ዛሬም ልክ በዘካርያስ

ዘመን የነበራቸውን ሁኔታ አልቀየሩም። እግዚአብሔር ሊሰጠን የሚፈልገው ሦስት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ብርታት፣ ቁ. 5። እግዚአብሔር ሊሰጠን የሚወደውን ብርታት ስንቀበል ምንም ዓይነት ጠላትና ማናቸውንም ተቃውሞ ሁሉ በድል እንወጣለን፣ 4፡6። በሕይወታችን ውስጥ በሁሉም አቅጣጫ የራሳችን ያልሆነ ብርታት እንለማመዳለን።

2. ጥበቃ፣ ቁ. 8። ምን ዓይነት ጥበቃ እንደሚያሻን እርሱ ከኛ ይልቅ ያውቃል። ጥቃቶች የሚመጡብን ከየትኛው አቅጣጫ እንደሆነም ያውቃል። ይህንን ዋስትና በመያዝ «ከክፉ ሁሉ አድነን» ብለን ልንጸልይ እንችላለን።

3. ማስተዋል፣ ቁ. 10። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ኢየሩሳሌም የሚለው ስም የሚያመለክተው ከተማይቱን፣ ሕዝቡን ወይም የእያንዳንዱን ሰው ልብ የትኛውንም ቢሆን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ተግባራዊ ማድረግን በሚመለከት ምንም ለውጥ አያመጣም። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት በረከት የሚያስገኝ እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገንን ማስተዋል ይሰጠናል።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. መልእክቱ የተነገረው ስለ ማን ነው? ቁ. 1
2. እግዚአብሔር የተገለጸው እንዴት ነው? ቁ. 1
3. ኢየሩሳሌም ለጠላቶች ምን ትሆናለች? ቁ. 2
4. ኢየሩሳሌምን ለመውረር ምን ያህል አዳጋች ነው? ቁ. 3
5. በጦር ሠራዊቱ ላይ ምን ይደርስበታል? ቁ. 4
6. አይሁድ ምን ይግራሉ? ቁ. 5
7. ምንም ነገር የማይነካው ማን ነው? ቁ. 6
8. ኢየሩሳሌም ከይሁዳ ይበልጥ ትመረጣለች? ቁ. 7
9. ጥበቃ የሚደረግለት ማን ነው? ቁ. 8
10. ሁሉም የሚያለቅሱት ለምንድነው? ቁ. 10

የውይይት ጥያቄዎች

1. ይህ ምዕራፍ በፋርስ የቀሩትን አይሁድ የሚረዳቸው እንዴት ነው?
2. ምዕራፉ ሊኖረው የሚችለው ምን ዓይነት አተረጓጎም ነው?
3. ክርስቲያን ብርቱ የሚሆነው መቼ ነው?
4. ጥበቃ ማለት ምን ማለት ነው?
5. ሕዝቡ ያለቀሰው ለምንድነው?

የቤት ሥራ

ምዕራፍ 12 ን ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ አንብቡት። ቢቻል ሃሳባችሁ እንዲቀሰቀስና እንዲነቃቃ የተለያዩ ቅጂዎችን በመጠቀም አንብቡት። በተሰጣችሁ ማብራሪያ ላይ የራሳችሁን ማስታወሻ ጨምሩበት።

ምዕ. 13 ስለ <u>መከራ</u> ይናገራል። ለሚቀጥለው ጥናት ለመዘጋጀት ምዕራፉን በሙሉ አንብቡት።

ጥናት አሥራ አራት - ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ፈተና

ክርስቲያኖች እውነትንና ውሸትን በትክክል ለይተው ሊያውቁ እንደሚችሉ የተሰፋ ቃል ተሰጥቷቸዋል፥ 1ኛ ዮሐ. 2፡27። በእያንዳንዱ ክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይኖራል። እውነትንና ውሸትን ለይተን እንድናውቅ የሚያስተምረንም ይኸው መንፈስ ቅዱስ ነው። ከመነምጀት የሚመጣን ፈተናና ከእግዚአብሔር የሚመጣን ፈተና የሚለያቸውም ነገር ይህ ነው። የተሳሳተን ነገር ለመሥራት መመኘት ከመነምጀት የሚመጣ እንጂ ከእግዚአብሔር የሚመጣ ፈተና አይደለም።

ከመነምጀት የተነሳ የሚመጣ ፈተና በጭራሽ ከእግዚአብሔር አይደለም፥ ያዕ. 1፡13። እግዚአብሔር ክፉ በመሥራት ሊፈተን አይችልም። ስለዚህ ሌሎችም ደግሞ በክፉ እንዲፈተኑ አይፈቅድም። ከመነምጀት የሚመጣ ፈተና ከሰይጣን ሲሆን ራሱ ግን ኃጢአት አይደለም። ይህ ስህተትን ለመሥራት መጋበዝ ነው። ከዚህ ስህተትን ለመሥራት መማረክ ጋር እግዚአብሔር መውጫውን ያዘጋጃል፥ 1ኛ ቆሮ. 10፡13።

ከሌላ አንፃር ደግሞ እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ይፈትናቸዋል፥ ይህም ሁላችን መረዳት የማንችለው ነገር ነው። እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው ከአንድ አቢይ ምክንያት የተንሳ ሊሆን ይችላል፥ ይኸውም የተልዕኮውን ጥራት ለዓለም ማሳየት ይፈልግ ይሆናል። እግዚአብሔር አብርሃምን ፈትኖታል፥ ዘፍ. 22፡1። የአብርሃም ልብ ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር። እግዚአብሔር አዳምና ሄዋንን ፈትኗቸዋል፥ እነርሱም እግዚአብሔርን ለማስቀደም ዝግጁ እንዳልነበሩ ፈተናው አሳይቷል።

መሠረታዊ ነጥቦች

በምዕ. 5 ውስጥ 6ኛውንና 7ኛውን ራእዮች አንብበናል። እነዚህም ራእዮች ስለ እግዚአብሔር ቃል ኃይል ነገረውናል፥ 5፡1-4። በራሪው ጥቅልል ብራና በግለሰቦች ኃጢአት ላይ የፍርድ ቃል አውጇል። የተለመዱት ኃጢአቶች ግለትም መዋሸትና ስርቆት ከምድሪቱ ይወገዳሉ። ከዚያም ኃጢአት ሁሉ ይወገዳል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ማሕበር ያጠራል።

ምዕ. 13 ውስጥ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትምህርት ይገኛል። እግዚአብሔር ሕዝቡ በመንፈስና በእውነት እንዲያመልኩት ይፈልጋል፥ ዮሐ. 4፡24። በምዕ. 13፡1-6 ውስጥ የሐሰት አምልኮ ተወግዟል። እግዚአብሔር ይህንን ከሕዝቡ ማህበር ጠርጎ ለማውጣት ተስፋ ሰጥቷል። ምዕ. 12፡10-14 ስለሕዝቡ ንስሐ ይነግረናል። ይህ ከምዕ. 13፡1-6 መንፃት ቀደም ብሎ መደረግ አለበት።

ምዕ. 13፡1-6 የሐሰት ነቢያትን እንደሚያመለክት ሁሉ 13፡7ም በመጀመሪያው የሚያመለክተው መልካሙን እረኛ ሳይሆን ሐሰተኛውን እረኛ ነው። ክፍለ ምንባቡ በግቴ. 26፡31 ና በማር. 14፡27 ውስጥ በተጠቀሰበት ወቅት በኢየሱስ ሐሳብ ውስጥ

የነበረው አንዱ ጥቅስ ብቻ ሳይሆን ዘካ. ምዕ. 13፡7-9 ጭምር ነበር። ይህም በእርግጥ የእርሱ የሆኑትን ለማረጋገጥ የተደረገውን የሕዝቡን መፈተን የሚመለከት ነው።

ማብራሪያ

ምንባቡን ማብራራት ከመጀመራችን በፊት ምዕ. 13፡1-6 የብሉይ ኪዳንን ነቢያት በሙሉ የሚመለከት ነው የሚለው አተረጓጎም የተሳሳተ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ይህ አተረጓጎም ከክፍለ ምንባቡ፤ ከመጽሐፉ መልእክትና ከተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር አይስማማም። ምዕ. 13፡1-6 የነቢይነትን አገልግሎት የሚያወግዝ አድርገው ሊተረጉሙት ሙከራ የሚያደርጉትን ምሁራን የክፍለ ምንባቡን ትርጉም አልተገነዘቡም።

13፡1-6 ቁ. 1 ከ12፡12-14 ጋር በጣም የተያያዘ መሆኑ ግልጽ ነው። በ12፡12-14 ውስጥ የተገለጠው የዕንባው ምንጭ እንዲፈልቅ ያደርጋል። ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የተጠቀሰው «በዚያ ቀን» የተሰኘው ሐረግ መለስ ብሎ 12፡5 ን የሚያመለክት ይሆናል። የምንጩ ዓላማ ከኃጢአት ማንፃት ነው፥ ማር. 10፡45። የተጠቀሰው ልዩ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ይልቅ ግዑዝ ነገሮችን ማምለክ ነው።

ምንጩ ምን እንደሚያደርግ ተመልከቱ፥ 1. ጣዖታትን ያጠፋል፥ 2. ሕዝቡን ወደ ጣዖት የወሰዱትን ሐሰተኛ ነቢያት ያስወግዳል፥ 3. እንዲሁም ጣዖታትን የመፈለግ ሐሳብ ያጠፋል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከተራ ውጫዊ የሆነ መንፃት አልፈው ጥልቅና ዘለቄታ ያለውን ነገር ይጠቁማሉ። ይህ ውስጣዊ ተሃድሶ በኋላ የሚመጣውም ነገር ደግሞ መሠረት ነው።

ውስጣዊ ለውጥ የሚያስደንቅ ስለሆነ ልጆቻቸው በሐሰተኛ ትንቢት ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ወላጆች ወሳኝ እርምጃዎችን ይወስዳሉ። በሐሰት ትንቢት ውስጥ የተሳተፉት የውሸት ልብሳቸውን አውልቀው በመጣል ጨርሶ ይህንን መሰል ነገር አድርገን አናውቅም ብለው ይክዳሉ። ሰውነታቸውን የጠበሱት ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ ገበሬዎች እንጂ ነቢያት አይደለንም ብለው ይክዳሉ።

13፡7-9 ቁ. 7 ሁለት የአተረጓጎም ደረጃዎች እንዳሉት ማቴ. 26፡31 ና ማር. 14፡27 በግልጽ ያሳዩናል። በእርግጥ ዘካርያስ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚናገረው ስለ ሐሰተኛ ነቢይና በጎች ነው። በምዕራፉ ሁለት ክፍሎች ውስጥ የተገለጸው መንፃት ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ነው። በቁ. 15፡9 ላይ «መንፃት» ይገኛል፥ አንዱ መንፃት በውሃ ሲገኝ ሌላው በእሳት ይገኛል። የሁለቱም ውጤቶች ተመሳሳይ ናቸው፥ ይኸውም ሐሰት ይወገዳል፥ ሐቅ የሆነው ነገር የእግዚአብሔርን ክብር ይገልፃል፥ 2ኛ ቆሮ. 3፡18። በቁ. 9 ውስጥ «መፈተን» የሚለው ወይም ተመሳሳይ ቃል አራት ጊዜ ተጠቅሷል።

በቁ. 7 መጨረሻና በቁ. 8 ላይ የተጠቀሰው «መበተን» አዲስ ተስፋ እንዳስገኘ ሁሉ በእረኛው ላይ የተደረገውም ጥቃት አዲስ ተስፋ ያስገኛል። የአንድ ሰው በሌሎች ፈንታ መከራ መቀበል በመላው ብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ጭምር በብዛት ተጠቅሶ ይገኛል። ለምሳሌ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ሲል መከራ ተቀብሏል። የሌዋውያን

መሥዋዕቶች መሥዋዕቱን ባቀረበው ሰው ፈንታ ይሰዉ ነበር። በኢሳ. 53 ውስጥ የተጠቀሰው አገልጋይ ሌሎችን ለማዳን ተሰቃይቷል። እዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ እረኛው ይሞትና መንጋው ይተርፋል፥ ዮሐ. 10። አልፎ አልፎ አቢይ ትምህርቱ ግልጽ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በጨረፍታ ብቻ ተጠቅሷል። በምዕራፉ የመጨረሻ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ላይ የተጠቀሱትን ውጤቶች የሚያስገኘው ይህ በሌሎች ፈንታ መከራ መቀበል ነው።

ማጠቃለያ

በኢየሩሳሌም የመነጨው ምንጭ መለኮታዊ መነሻዎችና ተግባሮች አሉት። ሕዝ. 47 ንም ያሳስበናል፥ በሕዝቅኤል ውስጥ የሚገኘው ክፍለ ምንባብ ምንጩ በሚያዳርሰው ሥፍራ ላይ ያተኩራል። በዘካርያስ ውስጥ ያለው ኃይል ተጠቅሷል። የሥነ ምግባር መንፃት የማስገኘት ችሎታ አለው። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህም ከኃጢአታቸውና ከጣዖት አምልኮአቸው መንፃት ለሚፈልጉ ሁሉ አገልግሎቱን እንደሚሰጥ አዲስ ኪዳን ያስረዳናል።

በሐሰተኛ ነቢያት ላይ ጥንቃቄ ስለማድረግ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አዲስ ኪዳንን ሁሉ ያዳርሳል። ክርስቲያኖች ካሏቸው ጠላቶች መካከል በጣም አደገኞቹ እነዚህ ናቸው። የእግዚአብሔርን ቃል በውሸት ይለውጣሉ። ከዚያም ሥነ ምግባርን ቅጥፈት ውስጥ በሚጨምሩ የሐሰት የተሰፋ ቃሎች ይተኩታል። እነዚህ ትምህርቶች በአንድ የታመነ ፈተና ተለይተው ሊታወቁ ይችላሉ። በተቀባዮቹ ሕይወት ውስጥ ሥነ ምግባራዊ ኃይል አይታይበትም።

ፈተናው እህልን ከመውቃት ጋር ይመሳሰላል። ገለባው በኖ ሲጠፋ ፍሬው እህል ይቀራል። እውነተኛው እህል በምን ተለይቶ እንደሚታወቅ አስተውሉ፥ በምዕራፉ መጨረሻ ላይ በሚገኙት ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሦች አጥኑ። ይህ በቁ. 1 ና 2 ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት እግዚአብሔር ከሚያደርገው ነገር ጋር ሊያያዝ ይችላል።

ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

ይህንን ምዕራፍ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ጎን ለጎን አብረውት ሊሄዱ የሚችሉ ታሪካዊ ሁኔታዎች በመጽሐፈ አስቴርና በብዙ ሌሎች የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪኮች ውስጥ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ መልእክቱ በነዚህ ምሳሌዎች ላይ ብቻ እንዲወሰን ማድረግ አስፈላጊ አይደለም።

የእግዚአብሔር ይቅርታ በምንም ነገር የማይወሰን ነው። ንስሐ ከይቅርታ መቅደም እንዳለበት መገንዘብ ይጠቅማል፥ ምዕ. 12፡10-14። ንሥሐ በምንገባበት ወቅት ሁሉ መለኮታዊው ምንጭ በኛና በእግዚአብሔር መካከል ከሚገባ ማንኛውም ነገር ሊያነፃን የሚያስችል የተትረፈረፈ ብቃት አለው። ይህ መለኮታዊ ይቅርታ ከሌለ ተብትበው ከሚያሥሩንና ከእግዚአብሔር ከሚያርቁን ነገሮች ማምለጥ የሚያስችል ነፃነት የለም።

ዓለም በሐሰተኛ ነቢያት የተሞላች ናት። እነዚህ ነቢያት የሚናገሩት ነገር ላለመስማት መከላከል የምንችልበት ዘዴ የለም። በብዙ የተለያዩ ሽፋኖች ሥር ሆነው ወደ እኛ ይመጣሉ። እኛ ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር ትምህርታቸው በእስተሳሰባችንና በሕይወታችን ውስጥ ሥፍራ እንዳያገኝ መቆጣጠር ነው። በግድየለሽነት የእነዚህም ሰዎች አንዳንድ ሃሳቦች እንዳንቀበል በትጋት መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

ፈተና ሁሉ ወደ እግዚአብሔር በይበልጥ ሊያቀርበን ይችላል። ፈተና ስለግንወድ ብቻ አንቀበልም እንዳንል መጠንቀቅ ይገባናል። እግዚአብሔር በሚሠራው ነገር ውስጥ ሁሉ ምንም ዓይነት ጎጂ ዓላማዎች የሉትም። ፈተናው ገለባውን ብቻ ወደ ውጭ ሲጥል እውነተኛው ፍሬ የቱ እንደሆነና የሚገኝበትን ሥፍራ ጨምሮ ይገልፃል። በፈተናው ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ያበረታል፥ ይጠብቃል።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሕዝቡ የሚነፁት ከምንድነው? ቁ. 1
2. ከመካከላቸው የሚወገደው ምንድነው? ቁ. 2
3. የሚጠፋው የምን ፍላጎት ነው? ቁ. 2
4. በቁ. 3 ላይ የተጠቀሰው ምን ዓይነት ነቢይ ነው?
5. እነዚህ ሰዎች ነቢያቱን የመሰሉት ለምንድነው? ቁ. 4
6. ይህ የቀድሞ ሐሰተኛ ነቢይ የሚያቀርበው ሰበብ ምንድነው? ቁ. 5
7. ሊቆስል የቻለውስ እንዴት ነው? 1ኛ ነገ. 18:28
8. በቁ. 7 ላይ ጥቃት የደረሰበት ማን ነው?
9. የሚወድቁት ስንት ሰዎች ናቸው? ቁ. 8
10. ለተቀሩት ሰዎች እግዚአብሔር ምን ያደርግላቸዋል? ቁ. 9

የውይይት ጥያቄዎች

1. በዘካ 13:1-6 ውስጥ አብረው ሊሄዱ የሚችሉት ሁለት ሃሳቦች ምንና ምን ናቸው?
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንጭ ምሳሌ የሚገኘው የት ነው?
3. ምንጊዜም የመንፃት አቢይ ውጤት ምን ይሆናል?
4. በዘካ 13:7፥ በማቴ. 26:31 ና በማር. 14:27 መካከል ምን ግንኙነት አለ?
5. ከዘካ 13:9 ጋር የሚመሳሰሉት ሌሎች ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?

የቤት ሥራ

ቢቻል የተለያዩ ቅጂዎችን በመጠቀም ምዕ. 13 ን ደጋግማችሁ ብዙ ጊዜ አንብቡት። የተሰጠውን ማብራሪያ አጥኑ። የራሳችሁን ማስታወሻና አስተያየት

ጨምሩበት። ይህ ምዕራፍ በሕይወታችሁ ላይ ምን ለውጥ ማምጣት እንዳለበት ራሳችሁን ጠይቁ።

ጥናት አሥራ አምስት - ምዕራፍ 14፡1-11

ተዓምራዊ መሰናዶ

ከእግዚአብሔር ብዙ ሥራዎች መካከል አንዱ ለሕዝቡ የሚያደርገው ልዩ እንክብካቤ ነው። ይህም ማለት የሚያስፈልጋቸውን ነገር መስጠት ብቻ ማለት ሳይሆን እርሱ እንደሚፈልገው መሆን እንዲችሉ ማድረግ ማለትም ነው። ራሳቸውን ከዓለም እንዲደብቁ የእርሱ ዕቅድና ዓላማ አይደለም። በዓለም መንፈስ ሳይማረኩ እንዲመላለሱበት ያስችላቸዋል። እጅግ አስፈላጊው ነገር ያለንበት ሥፍራ ሳይሆን የማን መሆናችን ነው።

እግዚአብሔር ፀንተን ለእርሱ እንድንቆም የሚያስፈልገንን ፀጋና ብርታት ይሰጠናል። በ586 ዓከልበ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለባቢሎን አሳልፎ ሰጥቷታል፥ ቢሆንም ከነበረው ሁከት ሁሉ ኤርምያስን አድኖታል። ኤርምያስ በየጊዜው በተደጋጋሚ በመከራ ተከቧል፥ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር መጽናናትና ብርታት ሰጥቶታል።

እግዚአብሔር ሰዎችን በንስሐ ወደ ራሱ ለማቅረብ ያለማቋረጥ በምድር ላይ ይፈርዳል። ፍርዱ ለመጨረሻው ዘመን ብቻ አይደለም። በዚህም ወቅት የገዛ ራሱ ሕዝብም የፍርዱ ተካፋይ ሆኗል። ሆኖም በነዚህ ወቅቶች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ልዩ መሰናዶ ሊያደርግ ችሏል፥ ማቴ. 10፡16-20። እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን በግብፅ ይኖር ለነበረው ሕዝቡ ይህንን አድርጓል።

መሠረታዊ ነጥቦች

በዘካ. 14፡1-11 ውስጥ «ኢየሩሳሌም» የሚለው ስም ቢያንስ አምስት ጊዜ ተጠቅሷል። የሚፈፀሙት ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተማና ሕዝብ ማህበር ጋር የተያያዙ ናቸው። ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ዐይን ልዩ ከተማ ብትሆንም ከመወረር አታመልጥም። ሁለቱ የ701 ዓከልበና የ586 ዓከልበ ምሳሌዎች ይህንን ለመግለፅ በቂ ናቸው፥ ኢሳ. 36-39 ንና ኤር 52ን ተመልከቱ። የመጨረሻው ማረጋገጫ በ70 ዓ.ም. የከተማይቱ በሮማውያን መደምሰስ ነው።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚያስበው ለተደራጀው የሕዝቡ ማሕበር ማለትም ለከተማይቱ ሳይሆን የእርሱ ለነበሩት ሰዎች ነው። በስሙ እየተጠሩ ያልተለወጡት ሰዎች ድክመት በከተማይቱ ላይ ፍርድ ያመጣባታል። በ586 ዓከልበ እግዚአብሔር ቅሬታውን ሕዝብ ወደ ባቢሎን ወስዶታል፥ በኋላም ልጆቻቸውን ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ አምጥቷቸዋል።

በፋርስ የነበሩት ሃይማኖተኛ የአይሁድ ቅሬታ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ሁኔታ ሳይረበሹ አልቀሩም። ኢሳ. 59፡1-8 ይህንን የመሰሉ ሁኔታዎች ያንፀባርቃል። እግዚአብሔር የሚሆነውን ነገር በሚገባ እንደሚያውቅ ነቢዩ ዘካርያስ ያረጋግጥላቸዋል። እግዚአብሔር ከተማይቱን ለማጥራትና የእርሱ የሆኑትን ሰዎች ለማዳን ይፈረድባታል።

ማብራሪያ

14፡1-5 የምዕራፉ አቢይ ትምህርት በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ተጠቁሟል፥ ይኸውም በእግዚአብሔር ፍርድና በአንዲት ልዩ ከተማ ላይ የሚያተኩር ነው። በቁ. 1-2 ውስጥ የተመዘገቡት ድርጊቶች ከታሪክ አንፃር ብዙ ጊዜ ፍፃሜ ያገኙ ስለሆነ የተለያዩትን ዘመናት ሊያመለክቱ ይችላሉ። በከተማይቱ ውስጥ የነበሩት ክፋቶች በቸልታ አይታለፉም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእግዚአብሔር ምሕረት ጣልቃ ይገባል። ቁ. 3 ለቁ. 4-5 የተሰጠ አጭር መግቢያ ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጎን ይቆማል። በምድረ በዳ በነበሩበት ዘመን ራሱን በገለጠላቸው አኳኋን እግዚአብሔር ራሱ ወደ እነርሱ ይቀርባል። ቁ. 2 እንደሚጠቁመው ኃጢአተኞች ይቀጣሉ። ከዚያም እግዚአብሔር ለተቀሩት ማምለጫ ያዘጋጅላቸዋል፥ ቁ. 4። ትኩረት የተደረገው በሽሽታቸው ላይ ሳይሆን በከተማይቱ ላይ ከሚመጣው ፍርድ እንዲያመልጡ እግዚአብሔር ባሰናዳላቸው መንገድ ላይ ነው።

14፡6-11 ቀጥሎ ሦስት ነገሮች ተገልፀዋል። እነዚህም፡- ቁ. 6-7 መጠለያ፥ ቁ. 8-9 ብቃትና ቁ. 10-11 ዋስትና ናቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡን የማዳኑ ሁለተኛ ደረጃ ውጤቶችም ናቸው። ከፍርድ የሚያመልጡበት መንገድ ስለተዘጋጀላቸው ቀጥሎ የተጠቀሱትንም ደግሞ ይሰጣቸዋል፡-

1. እግዚአብሔር የሚንከባከባቸውንና የሚያጽናናቸውን ብርሃን ይሰጣቸዋል። ምናልባት በዚህ ሥፍራ ደግሞ የተስተጋባው የኢያሱ ዘመን የፀሐይ መቆም ድል ሳይሆን አይቀርም። ተፈጥሮአዊ መሰናክል የሆኑት ብርድና ጨለማ እንኳ ይቆጠራሉ።

2. ቁ. 8 የሚናገረው ስለ ተፈጥሮአዊ ውሃ አለመሆኑን ምናልባት ቁ. 9 ይጠቁማል። ትርጉሙ ማንኛውም ቢሆን እግዚአብሔር ተዓምራዊ ብቃት ይሰጣል። ይህም ዘመነ መንግሥቱን ያራዝመዋል።

3. የቁ. 10 ትርጉምም ቁ. 11 ላይ ተሰጥቷል። እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው አስለቅቆ ፋታ ይሰጣቸዋል። «ምድሪቱ እንደ አረባ ትሆናለች» ማለት ጠላቶች ማንም ሳያያቸው ወደ ከተማይቱ መቅረብ እንዳይችሉ ለጥ ያለች ሜዳ ትሆናለች ማለት ነው። ከተማይቱ ከቀድሞ ይበልጥ በጣም ከፍ ከፍ ትላለች፥ እንዲሁም በጣም ትሰፋለች።

ክፍለ ምንባቡ የያዘው መሠረታዊ ሐሳብ ይኸውም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገው ተዓምራዊ መሰናዶ ለዘለቄታው የማይለወጥ ዋጋ አለው። የዘካርያስ ዘመን ሕዝብ መስማት እንዳስፈለገው እኛም ልንሰማው ያሻናል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ማዳኑና የሚያስፈልገውን መስጠቱም ታሪካዊና በተግባር የተፈተነ ሐቅ ነው። ከእነዚህ ሐሳቦች ጋር የጥቅሶቹን ቀጥተኛ ፍፃሜ እንደያዝን የደብረ ዘይት ተራራ መሰንጠቅ፥ የንፁህ ውኃ መፍለቅና የኢየሩሳሌም አካባቢ ደልዳላ ሜዳ መሆን ተጨማሪ ፍፃሜ ሊኖረው ይችላል።

በመጀመሪያ ሁኔታ ላይ ብቻ ከሚገባ በላይ ትኩረት በማድረግ ምንባቡ አሁን ለኛ የሚሰጠውን ትርጉም እንዳናሳጣው ጥንቃቄ መውሰድ ያሻናል።

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ሊፈርድ በአራሚ መንግሥታት ይጠቀማል የሚለው ትምህርት አዲስ አይደለም። አሥሩ ነገዶች በ722 ዓክልበ በአሦርና የተቀሩት ሁለት ነገዶች ደግሞ በ586 ዓክልበ በባቢሎን ተቀጥተዋል። ይህንን የመሰለው ዘመን በሚመጣበት በማንኛውም ወቅት እግዚአብሔር በእርግጥ የእርሱ የሆኑትን ከፍርድ ያድናቸዋል።

ብሔር መሆን ደረጃ እስኪደርሱ እንዲያድጉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ግብፅ ሲልካቸው ልዩ እንክብካቤ አድርጎላቸዋል። እግዚአብሔር ማምለጫ እንደሚያዘጋጅላቸው እነርሱና ጠላቶቻቸውም ጭምር ያውቃሉ፥ 1 ቆሮ. 10፡13። እርሱ በእምቢተኞቹ ላይ ከሚያመጣው ጥፋት እንዲያመልጡ ለመምራት መላእክቱ እረኞቻቸው ሆነው ይጠብቋቸዋል።

ኃጢአት ምንጊዜም የሚያፈራርስ ነው። ዘወትር አፍራሽና በታኝ ነው። ከፍርዱ በኋላ አጥፊ የሆኑት የኃጢአት ውጤቶች ሁሉ ይወገዳሉ። የእግዚአብሔር በረከቶች መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆኑ ቁሳዊም ናቸው። በአካባቢው የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ይነካቸዋል። የማያስደስት፣ የሚያስፈራና አደገኛ የሆነ ነገር ሁሉ ይወገዳል።

ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ልዩ በሆኑ መንገዶች እንዲሠራ ልንጠባበቅ ይገባል። እኛ የእርሱ ስንሆን በዕቅዶቹና በአላማዎቹ ውስጥ ልዩ ሥፍራ ስለሚኖረን የተለዩ ነገሮችን ሊያደርግልን እንደሚፈልግ የሚገልፅ ቀዳሚ ዋስትና እናገኛለን። እግዚአብሔር ያለማቋረጥ እንዲሠራ ልንፈቅድለት ዝግጁ መሆናችንን በጥንቃቄ መመርመር አለብን። የሥራው ተካፋይ ለመሆን ፈቃደኛ ባለመሆን ሥራውን አስተጓጉለን ይሆናል። ስለዚህ እርሱ በሌሎች ሊገለገል ስለሚችል በረከቱ ያመልጠናል።

ስንዴውን ከገለባው ለመለየት ፍርድ የሚጀምረው ከእግዚአብሔር ቤት ነው፥ በዘካ. 14፡1-11 ውስጥ የእግዚአብሔር ቤት በኢየሩሳሌም ከተማ ተመስሏል። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች ይገኛሉ። የእግዚአብሔር ልጆች አይፈረድባቸውም። ፍርድ የሚመጣው የእግዚአብሔር ልጆች ባልሆኑት ሰዎች ላይ ነው። ቅጣት የሚቀበሉት ንስሐ አንገባም ያሉ ልጆች ናቸው።

ታምራት አድራጊው እግዚአብሔር ብርድና ጨለማ የሆነውን ነገር ሁሉ ከሕይወታችን ሊያስወግድ ይችላል። በሀሙ ድንጋይ ድንገት ንፁህ ውሃ ሊያመነጭ ይችላል። ወራሪዎችን ይሸሽጉ የነበሩት ሸለቆዎች ደልዳላ ሜዳ ይሆናሉ። ይህ ሁሉ

እግዚአብሔር በሚሰጠን ይቅርታ ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚመጣ ነው። የኃጢአት ጎጂና አጥፊ ውጤቶች ሊወገዱ ይችላሉ። በአዲስ መልክ አንደገና የመጀመር ዕድል ይኖረናል።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኢየሩሳሌም ምን ትሆናለች? ቁ. 1
2. በከተማይቱ ውስጥ ስንት ሕዝብ ይቀራል? ቁ. 2
3. አሕዛብን የሚወጋቸው ማን ነው? ቁ. 3
4. እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊረዳ የት ይሆናል? ቁ. 4
5. ተራራው ለሁለት የሚሰነጠቀው ለምንድነው? ቁ. 5
6. ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆነው ማን ነው? ቁ. 5
7. የሚለወጡት ሕግጋት የትኞቹ ናቸው? ቁ. 6-7
8. ከኢየሩሳሌም መፍሰስ የሚጀምረው ምንድነው? ቁ. 8
9. ሕዝቡ ማንን ያመልካሉ? ቁ. 9
10. የኢየሩሳሌም ሁኔታ ምን የሚመስል ይሆናል? ቁ. 10-11

የውይይት ጥያቄዎች

1. በቁ. 2 ላይ የተጠቀሡ እውነተኛ አማኖች ናቸው?
2. እግዚአብሔር ራሱን ለሕዝቡ የሚገልጠው እንዴት ነው?
3. በቁ. 6-9 ውስጥ የተጠቀሱት ለውጦች ምንን ያመለክታሉ?
4. መላእክት ሕዝቡን የሚረዱት እንዴት ነው?
5. አማኞች በተለዩ መንገዶች ተባርከዋል?

የቤት ሥራ

በተለይ ምዕ. 14፡1-11 ን በቀላሉ መረዳት ያዳግታል። ክፍለ ምንባቡን ደጋግማችሁ በምታነቡበት ወቅት አቢይ መልእክቱን ለማግኘት ሞክሩ። በተሰጣችሁ ማብራሪያ ላይ የራሳችሁን ማስታወሻ አክሉበት።

ለሚቀጥለው ጥናት ዝግጅት ለማድረግ ምዕ. 14፡12-21 ን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ አንብቡት።

ጥናት አሥራ ስድስት - ምዕራፍ 14፡12-21

በቀል - ምርት - ቅድስና

ምንጊዜም የዓለምን ክፋት ስንመለከት እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ፍርድ ማምጣቱን ያለቅጥ አዘግይቶታል የሚል ግምት ላይ እንደርሳለን። በእኛ ላይ የማይጀምር ከሆነ አሁኑኑ ፍርዱን ሲጀምር ማየት እንወዳለን። ይሁንና እርሱ በትዕግሥት ይቆያል። ፍርዱ የማይታጠፍና እውነተኛ ነው። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ተነስተው የነበሩት ሰዎች በጣም ክፉኛ ይፈረድባቸዋል።

እግዚአብሔር ከአሕዛብም መካከል ደግሞ የቤተሰቡ አባላት የሚሆኑትን መሰብሰብ ይቀጥላል። ይህ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ባለው ዘመን ብቻ መፈጸም የነበረበት ነበር አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመን ውስጥ ሁሉ በተለያዩ መንገዶች ተግባራዊ ይሆን ነበር።

ከዚህም ጋር ተያይዞ ሕዝቡ ለፍፁም አገልግሎት ይለያሉ። ይህ የሚሆነው ምንም ስህተት ስለማይኖርባቸው ሳይሆን የሚያደርጉት ነገር ተቀባይነት ስለሚያገኝ ነው። ኃጢአት ግብ የለሽነትንና ዓላማቢስነትን ያስከትላል። ቅድስና የዚህ ተቃራኒ የሆነውን ነገር ያፈራል። ይህም የሚሆነው በአንድ ትንሽ ክልል ተወስኖ ሳይሆን እያንዳንዱን የሕይወታቸውን ክፍል ይነካል።

መሠረታዊ ነጥቦች

በፋርስ የቀሩት አይሁድ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላለው ሕዝቡ ምንም የተለየ ነገር የማያደርግለት መስሏቸው ይሆናል። ምናልባት ሦስቱ ዕረፍት ነሺ ጥያቄዎች የሚከተሉት ሳይሆኑ አይቀሩም፡-

1. እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን ለምን አይቀጣም?

2. እግዚአብሔር ሎሌችን ለምን አይሰበስብም? እንዲሁም

3. ሕዝቡስ የቅድስና ዕድገት የማይታይባቸው ለምንድነው?

የጥያቄዎቻቸው የመጨረሻ መልስ የሆኑት የእግዚአብሔር ዕቅዶች በዚህ ክፍል ተገልጠዋል። እነዚህ ሦስቱም ከበፊቱ በበለጠ አጠቃላይ መንገድ ተገለጡ አንጂ አዲስ ነገር አልነበሩም። እግዚአብሔር የሕዝቡን ያህል ስለ ጉዳዩ እንደሚያስብ አረጋግጠላቸዋል። አንድ ነገር ያደርግላቸዋል።

ውሱን በሆነ አመለካከት እነዚህ ትንቢቶች ሁሉ ገና ድሮ የተፈጸሙ ናቸው። በተጨማሪ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ምኞት ስፋትና ጥልቀት ስለሚገልፁ ሙሉ በሙሉ የሚፈጸሙ አይደሉም ልንል እንችል ይሆናል። ሌላ ተጨማሪ ቀጥተኛ ፍፃሜ ሊቀራቸውም የሚችልበት መንገድ ይኖራል። ይሁንና እነዚህ ነገሮች አሁን የሚሰጡንን ትምህርቶች በዚህ ላቢያ ማጣት የለብንም።

ማብራሪያ

4:12-15 የእግዚአብሔር ጠላቶች በሆኑት ሰዎች ላይ የኃጢአት ውጤቶች እያደር በጣም ግልፅ እየሆኑ ይሄዳሉ።

አጥፊዎቹ የኃጢአት ውጤቶች ጉልህ ሆነው ይታዩአቸዋል። እግዚአብሔር እየተበቀላቸው መሆኑን የሚደረገው ነገር ሁሉ ያረጋግጥላቸዋል።

በየትም ቦታ ክፉኛ ግርግር ይፈጠራል። አንዳንድ የይሁዳ ሰዎችም እንኳ ግራ ይጋባሉ። በኢየሩሳሌም ላይ በተደረገው ውጊያ ተሳታፊ ይሆናሉ፤ ይህ ሐሳብ የሚያስደንቅ ወይም ከዚህ በፊት ያላጋጠመን ነገር አይደለም። የእግዚአብሔርን ከተማ ለማጥፋት እነዚህ ሰዎች ባላቸው ሀብት ይጠቀሙበታል፤ ይኸውም ምናልባት ተጨማሪ የጦር እንስሳትን ሊገዙበት ይሆናል። እግዚአብሔር በቁ. 12 ላይ በነዚህ ሰዎች ላይ እንደፈረደባቸው ሁሉ በቁ. 15 ላይ በጦር እንስሶቻቸው ላይ ይፈርዳል። ይህ ምንባብ በይበልጥ የሚናገረው ስለ መጨረሻው ትልቅ ሴራ ሳይሆን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ እጃቸውን የሚያነሱ ሰዎችን ሁሉ ዕጣ በሚመለከት ነው።

14:16-19 ጠላቶች ወዲያው ወደ አምላኪነት ስለተለወጡ ቁ. 15ንና 16ን የሚያያይዝ ሐረግ ሊኖር ያስፈልጋል። በወንጌል መሰበክ አማካይነት ከተቀናቃኝነት ወደ ደጋፊነት ተለውጠዋል። እግዚአብሔርም የሚያመልኩት አምላክ ይሆንና በዘሌ. 23:33-34 በሚገኘው የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ተካፋይ ሊሆኑ ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዛሉ። በኢሳ. 2:1-5 ውስጥም ተመሳሳይ ሐሳብ ይገኛል። እግዚአብሔር ብቻ ሊሰጣቸው የሚችላቸው በረከቶች ከሌሎች አምላኮች ሊያገኙ የሚፈልጉ ሰዎች አሁንም ያሉ ቢሆንም እንኳ ሕይወታቸው በእሸዋ የተሞላ ምድረ በዳ ይሆንላቸዋል፥ ምርት አልባ ይሆናሉ።

14:20-21 ጠላት ቅጣት ይቀበላል። ከአሕዛብ መካከል የሚድኑ ሰዎች ሲኖሩ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላትም ምልክት ቅድስና ይሆናል። ፈረሶች የአሕዛብ መንግሥታት የጦር እንስሳት ናቸው። እነርሱም ለእግዚአብሔር የተለዩ ይሆናሉ። በቤተ መቅደሱ ውስጥ እጅግ የተናቁት አሮጌ ማሰሮዎች ይቀደሳሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ሁሉ የሚገኝ ማሰሮ አንድም ሳይቀር ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል። ሁሉ ነገር የተቀደሰ ይሆናል። ሁሉ ነገርም ስለሚቀደስ በቅዱስና በእርኩስ ነገር መካከል የነበረው ልዩነት ያከትማል።

«ነጋዴዎች» የተሰኘው ቃል ሌላው የከነዓናውያን ስም ነው። ስለዚህ የዐረፍተ ነገሩ ትርጉም፡- በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የቤተሰቡ አባላት ያልሆኑ አይኖሩበትም ማለት ነው። ቁሳቁሶች ሁሉ እንደሚቀደሱ ሕዝቡም ቅዱስ ይሆናል።

ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ምህረት በሌለው እኳኋን በሕዝቡ ላይ የሚነሱትን ሰዎች ይፈርድባቸዋል። በትንቢተ አብድዮ ውስጥ የምናገኘው መልእክትም ይህ ነው።

በተጨማሪ በኢሳይያስ፣ በኤርምያስና በዳንኤል ውስጥም በብዙ ሥፍራዎች እናገኛዋለን። ምንጊዜም እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመቅጣት ሊገለገልባቸው የመረጣቸው እነዚህን መንግሥታት መሆኑ እርግጠኛ ነው። ሆኖም ይህ እነርሱን ንፁህ አያደርጋቸውም። እነዚህ መንግሥታት ጭራሽ መጥፋት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ እንደተቀጡ ታሪክ በሰፊው ይመሰክራል።

እግዚአብሔር ከኃጢአት ኃይልና ቅጣት ያድናል የሚለው መልካም የምስራች ለአይሁድ ብቻ የተሰጠ አይደለም። አይሁድ ወደ ሌሎች አሕዛብ ለመላክ የተመረጡ ነበሩ። በእነርሱም አማካይነት ሌሎቹ አሕዛብ እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ይመጣሉ። እግዚአብሔር በተለይ የሚያተኩረው በ586 ዓክልበ ቤተ መቅደሱ ሲደመሰስ አይሁድ በኮበለሉባቸው ግብፅን በመሳሰሉ አገሮች ላይ ነው፥ ኤር. 42-44።

ሁሉ ነገር ለእግዚአብሔር እስኪለይ ድረስ ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ይሸነፋል። ርኩስ ነገር ሁሉ አይኖርም። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች በማሸነፍና ኃጢአትን በማስወገድ ድል አድራጊ ይሆናል። በፈረሶች አንገት ላይ የተንጠለጠሉትን ደወሎች የመሳሰሉ የጦር መሣሪያዎች ሁሉ እንኳ ለእግዚአብሔር ይቀደሳሉ።

ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

ፍርድን ማምጣት የእግዚአብሔር ፈንታ ነው። እግዚአብሔር ያደርጋል ብለን ልባችንን ሞልተን አርፈን መቀመጥ እንችላለን። ፍርድን እንዳለ በእግዚአብሔር እጅ ላይ ለመተው ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ኃጢአትን መገሰጽና ኃጢአት የሠሩ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ መምከር እንችላለን፥ ይሁን እንጂ ፍርዱን ለእግዚአብሔር መተው አለብን። እግዚአብሔር እኛ በምንፈልገው መንገድ በእፋጣኝ ላይፈርድ ይችላል፥ ፍርዱ ግን የማይቀር መሆኑን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

እግዚአብሔር ሌሎችን ከቤተሰቡ ጋር ሊቀላቀል በሚሰማራበት ወቅት እኛም የሥራው ተካፋይ መሆን አለብን። ሁሉ ሰምቶ እንዲያስተውል የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው። ከኃጢአት የመዳን መልእክት የአንድ ወይም የሁለት ሰዎች የግል ተስፋ አይደለም። እግዚአብሔር ሲሰራ እንደ ጠርሴሱ ሳዖል ያሉ ጠላቶች ወደ ሰባኪነት ተለውጠዋል።

እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ለይተን እንሰጠው። ሁሉ የእርሱ ነው፥ ስለዚህ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው እናድርግ።

አስራታችንን ብቻ ሳይሆን ያለንን ንብረት ሁሉ እንዲሁም እሁድን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ቀን ለእግዚአብሔር መቀደስ አለብን። ይህ ሲደረግ የረከሰ ነገር ሁሉ ይጠፋል። እግዚአብሔርም ፍፁም ገዢ ይሆናል።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. በቁ. 12 ላይ መከራ የተቀበለው ማን ነው?
2. ይሁዳ ኢይሩሳሌም የምትረዳው እንዴት ነው? ቁ. 14
3. የወራሪዎች ንብረት ምን ይሆናል? ቁ. 15
4. የተረፉት ሰዎች ምን ያደርጋሉ? ቁ. 16
5. እምቢተኞች የሚቀጡት እንዴት ነው? ቁ. 17
6. ቅጣት የሚቀበሉትስ እነማን ናቸው? ቁ. 18
7. የሚያከብሩት በዓል የትኛው ነው? ቁ. 19
8. የሚቀደሱት ነገሮች ምንድናቸው? ቁ. 20
9. የሚቀደሰው አንድ ተራ ነገር ምንድነው? ቁ. 21
10. ከቤተ መቅደሱ የሚወገደው ምንድነው? ቁ. 21

የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ የሚፈርደው መቼ ነው?
2. እግዚአብሔር ሲፈርድ ዓላማው ምንድነው?
3. በምዕ. 14፡16-19 ውስጥ ያለው ሐሳብ ምንድነው?
4. ቅድስና ማለት ምን ማለት ነው?
5. ምዕ. 14፡13-15 ገና ድሮ የተፈጸመው ከምን አንፃር ነው?

የቤት ሥራ

የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ እስክትረዱ ድረስ ዘካ. 14፡12-21ን ደጋግማችሁ ብዙ ጊዜ አንብቡት። የተሰጣችሁን ማብራሪያ አገናዝቡና የራሳችሁንም ማስታወሻ አክሉበት።

ለሚቀጥለው ሳምንት ጥናት ለመዘጋጀት ምዕ. 1-8ን ቢያንስ አንድ ጊዜ አንብቡ። ይህንንም በአንድ ጊዜ ልታደርጉት ብትችሉ በጣም ጠቃሚ ይሆናል።

መጽናኛ

መጽናናት ሲጠፋ ተስፋ የቆረጡት ይበልጥ ተስፋ ይቆርጣሉ። በመጨረሻም በመንገድ ላይ ይንጠባጠባሉ። ዓለም ተስፋ በቆረጡ ክርስቲያኖች የተሞላች ናት። መንፈሳዊ አቋማቸው ምንም ዓይነት ቢሆንም የሚያጽናኗቸው ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይገባል። ሌሎችን ማጽናናት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ኃላፊነት የሆነውም ከዚህ የተነሣ ነው።

ይህም ማለት ያጠፉትን ወይም የሚያጠፉትን ጥፋት በቸልታ እናልፈዋለን ማለት አይደለም። ይህ የተለየ ምክር ያስፈልገዋል፥ ኃጢአት የሠሩት ተስፋ ስለቆረጡ ሊሆን ይችላል። ይሁንና ከተግሳጽ ይልቅ መጽናናት የሚያስፈልጋቸው ክርስቲያኖች ሞልተዋል።

በተቻለን አቅም የማጽናናት ምክራችን ርዕሱን የለቀቀ መሆን የለበትም። ከርዕስ ውጪ የሆኑ የመጽናናት ምክሮች ሊያጽናኑ ቢችሉም ከዚህ የበለጠ ጠጋኝና ጠቃሚ የሚሆኑት ለሁኔታው ተስማሚ ሆነው ሲቀርቡ ነው። በዘካርያስ ውስጥ የሚገኘው መጽናናትም በጣም ተስማሚ የሆነበት ምክንያት ይኸው ነው። አጠቃላይ መጽሐፉ ርቀው ላሉት ሁሉ የመጽናናት አየር ይተነፍሳል።

መሠረታዊ ነጥቦች

በ538 ዓክልበ ፋርስ ባቢሎንን አሸንፋ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተራዋ በግሪክ እስከተሸነፈችበት 330 ዓክልበ ድረስ የዓለም ሐያል መንግሥት ሆናለች። ወዲያውም አንሻን የተባለችው አነስተኛ አገር ተወላጅ የነበረው ቂሮስ የድል አድራጊው ሠራዊት አዝማች ከሆነ በኋላ በመጨረሻ የኃያሉ የፋርሳውያን ግዛት መሪ ሆኗል። እርሱም የባቢሎናውያንን የአመራር መርሕ ለውጦ አይሁድ ወደ እሥራኤል እንዲመለሱ ፈቅዶላቸዋል። አንርሱም ከ538-536 ዓክልበ ባሉት ጊዜያት መካከል መመለስ ጀምረዋል።

በ522 ዓክልበ ዳርዮስ የተባለ ሌላ የፋርስ ንጉሥ ነግሧል። እርሱም በነገሠ በሁለተኛው ዓመት እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡት አይሁድ ሁለት ነቢያት ሐጌንና ዘካርያስን ልኮላቸዋል። እነዚህ ሁለት ነቢያት በአንዲት ከተማና በተመሳሳይ ጊዜ አገልግለዋል። ሁለታቸውም ለእሥራኤል ሕዝብ የነበራቸው አገልግሎት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ነበር፥ ይኸውም፦ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመገንባት እንዲበረቱ አጽናንተዋቸዋል።

በከፍተኛ ተስፋ ከፋርስ የተመለሱት ሰዎች ከ536-520 ዓክልበ ድረስ ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ምንም ሥራ አልሠሩም። ተስፋ መቁረጣቸውንም ለራሳቸው ትላልቅ ቤቶችን በመሥራት አካክሰውታል። ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅባቸው ሙሉ በሙሉ ተረድተው ነበር፥ ይሁን እንጂ የመሥራት ፈቃደኝነት አልነበራቸውም።

ተስፋዎቻቸውን በተግባር እንዲተረጉሙና ተባብረው በአንድነት ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ ሐጌና ዘካርያስ አጽናንተዋቸዋል።

ማብራሪያ

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የነበረው ዕቅድና ዓላማ በንስሐ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ነበረ። ይህ ካልሆነ ከፋርስ ወደ ይሁዳ መመለስ ከንቱ ነው፥ 1:1-6። ሕዝቡ ምንም ነገር ሊፈሩ አያስፈልግም። እግዚአብሔር መላውን ዓለም በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል፥ እነርሱም እንዲመለሱ ዕቅድ አውጥቷል፥ 1:7-17። ሕዝቡ አሁንም አንዳንድ ጠላቶች እንዳሉ አይካድም፥ ሆኖም እነዚህ ጠላቶች እግዚአብሔር ባዘጋጃቸው መዶሻዎች ይደቃሉ፥ 1:18-21።

የሕዝቡ መመለስ ኢየሩሳሌምን ታላቅ ከተማ ያደርጋታል፥ 2:1-5። እግዚአብሔር የከተማይቱን ጥራትና መጠን ያሳድጋል። ምናልባት እስከ ግብፅም ድረስ እንኳ በፋርስ ግዛት የተለያዩ ክፍሎች ሁሉ ውስጥ የተበተኑት አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳሉ፥ 2:6-13።

የምርኮው ዘመን አብቅቷል። የእግዚአብሔር መልእክተኞች እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያድን በሥራ መሠማራቱን የሚያበስሩ አዳዲስ ሁኔታዎችን ያሰማሉ፥ ኢሳ. 40:1-11። ሕዝቡ ይሰበሰባሉ የሚለው የመጀመሪያው ራእይ ሐሳብ ነው። ጠላቶቻቸው ይሸነፋሉ የሚለው ደግሞ የሁለተኛው ራእይ ሐሳብ ነው። ሕዝቡ የሚኖርባት አዲሲቱ ከተማ በጣም ሰፊ ትሆናለች፥ ይህ የሦስተኛው ራእይ ሐሳብ ነው።

የክህነት አገልግሎት ለ50 ዓመታት ተቋርጦ ነበር። ቤተ መቅደስ ላይኖር ካህናት መስዋዕቶችን ሊሰዉ አይችሉም። ሕዝቡም ጠቃሚነቱን ተጠራጥረዋል። ይሁንና እግዚአብሔር ኢያሱን አንጽቶት አንደገና ሊቀ ካህናት ሆኖ ማገልገል ይችላል፥ ምዕ. 3፤ ራእይ አራት። ይህ ለአገልግሎት መቀደስ በዘዳ. 29:1-37 ውስጥ ከተጠቀሰው ይልቅ በጣም ፍፁም ይሆናል።

እግዚአብሔር የሚያገለግሉትን ሰዎች በተለይም ኢያሱንና ዘሩባቤልን ላዘጋጃቸው ሥራ ብቃት እንዲኖራቸው በልዩ መንገድ ያስታጥቃቸዋል፥ 4:1-14፤ ራእይ አምስት። እግዚአብሔር በሐጌ አማካይነት ሕዝቡ ሥራ እንዲጀምሩ የሰጠውን ምክር ፍፃሜ ላይ ያደርሰዋል፥ 4:6-10። በራእይ አምስት ውስጥ ሌሎችን እንዲያገለግል ዘይት ከሚያቀርቡለት ዛፎች ጋር የተሰጠው መቅረዝ እንመለከተዋለን። ዛፎቹ ዘይት ለሰዎች እንዲሰጡ ጌታ እራሱ ዘይት ይሰጣቸዋል።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚፈልገው ንፁህ ካህናትንና አስተዳዳሪዎችን ብቻ ሳይሆን የጠሩ ሰዎችንም ይፈልጋል። ይህ በሁለት መንገዶች ተግባራዊ ይሆናል። የእግዚአብሔር ሕግ ምድሪቱን ይመራል፥ 5:1-4። እስካሁንም ድረስ እጅግ አጥፊ በሆኑት ኃጢአቶች በመዋሸትና በስርቆት ላይ ይፈርዳል። እግዚአብሔር ራሱ ኃጢአትን ከምድሪቱ ያጠፋል፥ 5:5-11። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት 6ኛና 7ኛ ራእዮች እነዚህ

ናቸው። እግዚአብሔር ኃጢአትን ሲያስወግድ ወደፊት የሚጥፋትና የመገዛት ኃይል አይኖረውም።

ይህ ትዕይንት አሁን የተዘጋጀው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲመለሱ ነው። ራእይ ስምንት ከራእይ አንድ ጋር ይመሳሰላል። ሠረገሎቹ የተበተነውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመሰብሰብ ይሠማራሉ፥ 6:1-8። በ586 ዓከልበ ሴዴቅያስ ከታሠረ ወዲህ አይሁድ ምንም ንጉሥ አልነበራቸውም። እግዚአብሔር አሠራሩን ለውጧል። እርሱ በካህናቱ አማካይነት መንፈሳዊና አስተዳደር ነክ ሥልጣን በግብር ላይ ያውላል፥ 6:9-15።

ዘካርያስ አሻግሮ የተመለከተው ፍፁም ንጉሥና ካህን የሆነውን መሢሑን ነበር።

በምዕ. 7 ውስጥ የዘካርያስ ሐሳብ የተለወጠው በይሁዳ ወዳደጉት ሰዎች ቡድን ነው። በፋርስ የነበረውን የምርኮ ዘመን ጨርሶ አልቀመሱትም። ቤተ መቅደሱ እንዲገነባ የተሰጡትን ትዕዛዞች እነርሱ ሰምተው ነበር፥ ይሁን እንጂ በዚያ ፈንታ ስላለፈው ነገር ግልቀስና መጮኽ ፈልገዋል፥ 7:1-7። ምርኮው በቅድመ አባቶቻቸው ዕምቢተኝነት ሳቢያ የመጣ መሆኑን አልተገነዘቡም። ሆኖም እግዚአብሔር ይቅር ሊላቸውና ሊያድሳቸው ዝግጁ ነው፥ 7:8-14። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ዕቅዶች ጋር እንቅስቃሴ በማድረግ ፈንታ ካለፈው ነገር አንላቀቅም ብለዋል።

ምዕ. 8 በምዕ. 2:1-5 ውስጥ የቀረበው የሦስተኛው ራእይ ማብራሪያ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ታላላቅ ነገሮችን አከማችቷል። ከሁሉ የሚበልጠው ደግሞ ገና ወደፊት ይመጣል። ለ50 ዓመታት ያህል ከተማይቱ ዕርቃኗን ቀርታ ነበር። በባቢሎን ሠራዊት ተደምስሳ ነበር፥ 2ኛ ነገ. 24። ይሁንና እግዚአብሔር ያጠፋውን ነገር መልሶ ማበጀት ይችላል። የሕዝቡን ሕብረት መልሶ በማደረጀት ይባርካቸዋል።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. በራእይ አንድ ውስጥ የታዩት አራት እንስሳት ምንድን ናቸው? 1:1-17
2. ራእይ ሁለት የሚገልጸው ስለ የትኞቹ ሁለት ነገሮች ነው? 1:18-21
3. ራእይ ሦስትስ የሚናገረው ስለ የትኛይቱ ከተማ ነው? 2:1-5
4. ራእይ አራት የቀረበው ስለማን ነው? 3:1-10
5. በራእይ አምስት ውስጥ የታዩት ሁለት ነገሮችን ጥቀሱ። 4:1-10
6. ልዩ ተስፋ የተሰጠው ለማን ነበር? 4:6-10
7. በራእይ ስድስት ውስጥ ምን ይፈፀማል 5:1-4
8. በራእይ ሰባት ውስጥ ኃጢአት የተወሰደው ወዴት ነበር? 5:5-11
9. በራእይ ስምንት ውስጥ የታዩት አራት ነገሮች ምን ምንድናቸው? 6:1-8
10. የምእ 8 አቢይ ትምህርት ምንድነው?

የውይይት ጥያቄዎች

1. የራእዮቹ ሁሉ መሠረታዊ ትርጉም ምንድነው?

2. የምዕ. 7 ልዩ ጥቅም ምንድነው?

3. የሐጌና የዘካርያስ መጻሕፍት የሚለያዩት በምንድነው?

4. የዘካ 1፡1-6 ና የ2፡6-13 የተለየ ጥቅም ምንድን ነው?

5. የዘካ 6፡9-15 ትርጉም ምንድነው?

የቤት ሥራ

ይዘቱ በአእምሮአችሁ ውስጥ ሰርፆ እስኪገባ ድረስ ምዕ. 1-8ን ደጋግማችሁ ልታነቡ ጥረት አድርጉ። በምታነቡበት ጊዜ የሚያጋጥማችሁን ጥያቄና የራሳችሁን አስተያየት ጻፉ።

የመጨረሻው ጥናት የሚያተኩረው በምዕ. 9-14 ላይ ነው። ይህ ክፍል ስለምን እንደሚናገር ጠቅለል ያለ ሐሳብ እንድታገኙ ምዕራፎቹን በሙሉ በአንድ ጊዜ አንብቡ።

ጥናት አሥራ ሰምንት - ምዕራፍ 9-14 ክለሳ

በራእዮች አማካይነት የተሰጠ ተስፋ

የወደፊቱን ሁኔታ ማየት ሊሳነን ያሁኑ ዕቅዶቻችሁ ሁሉ ግራ ይጋባሉ። ያሁኑ ሁኔታ ምንም ጥቅም የለውም ማለት አይደለም፥ እንዲያውም እግዚአብሔርን ማገልገል የምንችለው አሁን ነው። የወደፊቱ ሁኔታ ያሁኑ ሊኖረው የሚገባውን መልክ ያስይዘዋል። ለብዙ ሰዎች ያሁኑ ሁኔታ ከማንኛውም ነገር ጋር የተያያዘ አይደለም። መድረሻ ስለሌላቸውም ግራ የተጋቡና ዓላማ ቢስ ይሆናሉ።

እግዚአብሔር በዓለም ላይ እየሠራ መሆኑን እናምናለን። ስለዚህ የወደፊቱን ሁኔታ ስንመለከት፡- እግዚአብሔር ምን ሊሠራ ነው? ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን። እግዚአብሔር ዕቅዶቹንና ዓላማዎቹን ለነቢያቱ እንደገለጸላቸው ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንረዳለን። በእርግጥ ሁሉንም ነገር እናውቃለን ማለት ሳይሆን የወደፊቱ ሁኔታ በእርሱ እጅ ውስጥ እንዳለ ጥርጥር የለንም።

ዘካርያስ በምዕ. 9-14 ላይ በወደፊቱ ሁኔታ ላይ ገለጻ ያደርጋል። በእግዚአብሔር መንፈስም ተመርቶ እግዚአብሔር ወደፊት ምን እንደሚሠራ ዘካርያስ ያሳስበናል። ከነዚህ ዕቅዶች መካከል አንዳንዶቹ ግልፅ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ በመመሪያነት ደረጃ የተገለጡ ናቸው። ይሁንና ጥቃቅን ዝርዝር ሁኔታዎች ሰፊ ከሆኑት የእግዚአብሔር የድርጊት መርሆዎች ይበልጥ አሳሳቢ አይሆኑብንም።

መሠረታዊ ነጥቦች

ምዕ. 9-14 ምናልባት ከፋርስ ላልተመለሱት አይሁድ በተለይ የተፃፈ ሳይሆን አይቀርም። ይሁዳን ሲመለከቱ ችግሮችና ድከመቶች ሳይታዩባቸው አልቀረም። ስለዚህ በፋርስ መቆየት ለእነርሱ ጥቅም ያለው መስሎ ታይቷቸዋል። ከ586 ዓከልበ በኋላ ብዙ አይሁድ ወደ ግብፅ እንደሄዱ እናውቃለን። ዘካርያስ አነዚህንም ሰዎች በአእምሮው ሳያስብ አይቀርም።

እነዚህ ሰዎች ችግሮቹን ስለተመለከቱ ወደ ይሁዳ መመለስ አይፈልጉም። ዘካርያስ በምዕ. 1-8 ውስጥ ብዙ የማጽናናት ምክሮችን ሰጥቷቸዋል። በምዕ. 9-14 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል የሚለው ማረጋገጫ ላልተመለሱት አይሁድ ተሰጥቷቸዋል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍፁም ዕቅድ አለው፥ ሕዝቡም ሊባረኩ የሚችሉት ይህንን ዕቅድ ተግባራዊ ሲያደርጉ ነው።

ስለዚህ ሕዝቡ ከመመለስ በቀር ሌላ አማራጭ የላቸውም። እግዚአብሔርም መሢሑን የሚቀበል ቡድን በማዘጋጀት ላይ ነበር። ሕዝቡም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በቤተ መቅደሱ አገልግሎት፤ በክህነት አገልግሎትና ከብሉይ ኪዳን በሚያገኙት መመሪያ አማካይነት እምነታቸውን እንዲገነቡ የእግዚአብሔር ምኞት ነበር።

እግዚአብሔር በወቅቱ ሊመለሱ ፈቃደኛ ያልሆኑትን ሰዎች እንኳ ጨርሶ እንዳላገለላቸው መጽሐፈ አስቴር ይገልፃል።

ማብራሪያ

በምዕ. 9-14 ውስጥ ምንም ራእይ አይገኝም፥ ኢያሱና ዘሩባቤልም አልተጠቀሱም። ይሁን እንጂ እነዚህ ነጥቦች ማናቸውም የሐሳብ ወይም የፀሐፊ ለውጥ መኖሩን አይጠቁሙም። ርዕሱ የተለየ ስለሆነ በአገልግሎት ላይ የዋሉትም ቃላት ልዩ ናቸው። መሠረታዊው አቢይ ትምህርት አይለወጥም፥ ይኸውም ሕዝቡ ወደ ተመረጠችው የእግዚአብሔር ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ ማጽናኛ ምክር ተሰጥቶታል።

ይሁዳን ያሸነፏትና የዘረፏት ኃያላን መንግሥታት በሙሉ ይሸነፋሉ፥ 9:1-8። ይሁዳ የጦር ሠራዊት የላትም፥ ሆኖም እግዚአብሔር ይህንን ያደርጋል። ከዚያም የይሁዳ አዲስ ንጉሥ መሢሑ ይመጣል። በዚያ ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን መልሶ ያበጃል፥ 9:9-17። ሕዝቡ የሚናፍቀው የድልና የመታደስ በረከት የሚገኘው በኢየሩሳሌም እንጂ በፋርስ ዋና ከተማ በሱሳ አይደለም።

በፋርስና በግብፅ የሚኖሩት አይሁድ የአራሚ መንግሥታትን ኃይል በግልፅ ያያሉ። የእግዚአብሔር ሕዝብ በነዚህ ሰዎች ሃይማኖት ተሳስቶ ጠፍቶ እንደነበር አይካድም፥ 10:1-2። ሆኖም እነዚህ መንግሥታት ምንም ያህል ራሳቸውን ቢያተልቁም እግዚአብሔር ያዋርዳቸዋል፥ 10:3-5። ሕዝቡ በኃጢአት እንዳይጠመድ እግዚአብሔር ሥነምግባራዊ ብርታት ይሰጠዋል፥ 10:6-7። እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ፈቃደኛ ቢሆኑ ወደ አገራቸው ይመልሳቸዋል፥ 10:8-10። ምንም ነገር ሊያግዳቸው አይችልም፥ ወደ አገራቸውም መመለሳቸው ሙሉ በሙሉ ይሳካል፥ 10:11-12።

ይሁንና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት የረከሱ ሰዎች ምን ይሆናሉ? ማንም ይሁኑ ምንም በሁሳቸውም ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ይመጣባቸዋል፥ 11:1-3። በተጨማሪ እነዚህ ጥቅሶች የቀደመው ምዕራፍ መደምደሚያ ተደርገው ሊነበቡ ይችላሉ። እረኞችና መንጋቸው የረከሱ መሆናቸውን እግዚአብሔር በሚገባ ያውቃል፤ 11:4-6። በጎቹና እረኞቻቸው መመሳሰል ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሥልጣን አንቀበልም ስላሉ ከነርሱ ይርቅና ለፍርድ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፥ 11:7-14። ሆኖም ዋጋቢስ የነበሩት እረኞች ከእግዚአብሔር ፍርድ አያመልጡም፥ 11:15-17

ውጫዊ ገጽታዎችዋ ይህንን ቢመስሉም እንኳ እግዚአብሔር የተመረጠውን የሕዝቡን ማህበር ኢየሩሳሌምን አይከዳም ወይም ቸል አይልም፥ 12:1-5። ኢየሩሳሌምን የሚወሯት ድል ይደረጋሉ። የኢየሩሳሌም ድክመት እንዳለ ሆኖ እግዚአብሔር አሁንም ይንከባከባታል። በከተማይቱ ውስጥ ለሚኖሩት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ልዩ ጥበቃ ይደረጋል፥ 12:6-9። ከዚህም ጋር አብሮ የሥነምግባር ተሃድሶ ይመጣል። ሕዝቡም ከዚህ በፊት አይተውት በማያውቁት መንገድ ኃጢአታቸውን

ይመለከታሉ። በዚህ ጊዜ ንሥሐ ይገባል፥ 12:10-14። የእግዚአብሔርም ጥበቃ የተለወጠ ሕዝብ ያስገኛል።

ይህም ሕዝቡ ከዚህ ቀደም አይተውት የማያውቁትን ዓይነት መንፃት ያስገኛል። ሁለት ነገሮች ጨርሶ ይወገዳሉ። ጣዖት የሚባል ነገር ሁሉ ይጠፋና እግዚአብሔር ከሁሉም ነገር ይቀድማል፥ 13:1-6። የመለኮታዊ መከራ ውጤት ይገለጻል። ውጤቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዓላማ ማወቅ ይሆናል፥ 13:7-9። የእርሱን ፈቃድ የሚፈልጉና የሚኖሩበት በረከት ያገኛሉ፥ ፈቃዱን አንቀበልም የሚልት እነርሱም በተራቸው ተቀባይነት ያጣሉ።

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ መከራ እንዲመጣ ይፈቅዳል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ኃይልና በጠላቶቻቸው ላይ ደግሞ ቁጣውን ይገልፃል፥ 14:1-5። ይህ አዲስ ጣልቃ ገብነት ቁሳዊ መታደስንም ያስገኛል፥ 14:6-9። የእግዚአብሔርም ሕዝብ አዲስ ምኞት ያገኛል፥ 14:10-11።

የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማ የሚቃወሙ ይታገዳሉ፥ 14:12-15። እግዚአብሔር ሁሉን በቁጥጥሩ ሥር እንዳደረገ ይገነዘባሉ። ፍርዱም የፈጣሪን ሥራ ያሳስባቸዋል። በዚህ ወቅት ብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ፥ ሰዎች ከፋርስና ከግብፅ እግዚአብሔርን ሊያመልኩ ይመጣሉ፥ 14:16-19። የእግዚአብሔር በረከት የሕዝቡን ማሕበር በሙሉ ይነካል። ሁሉ ነገር ቅዱስ ይሆናል፥ 14:20-21። እግዚአብሔርና ሕዝቡም ፍፁም ይረካሉ።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር የሚፈርድባት የትኛይቱ ከተማ ናት? 9:1-8
2. ዘኪ 9:9 በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው የት ነው?
3. እግዚአብሔር ለተበተኑት አይሁድ ምን ያደርግላቸዋል? 10:6-12
4. በጎቹ ተቀባይነት ያላገኙት ለምንድነው? 11:7-14
5. ምዕ. 11:15-17 የሚናገረው ስለምንድነው?
6. የድሉ ውጤት ምን ይሆናል? 12:10-14
7. በዘኪ 13:1-6 ውስጥ የተወገደ ነገር መንድነው?
8. ሕዝቡ የተፈተኑት እንዴት ነው?
9. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ያደርጋል?
10. የዘኪ 14:20-21 አቢይ ትምህርት ምንድነው?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ተቅበዝባዥ የሆኑት እነማን ናቸው?
2. «ኢየሩሳሌም» የሚለው ቃል ትርጉም ምንድነው?
3. እረኞቹ እነማን ናቸው?
4. እግዚአብሔር ዛሬ ሕዝቡን የሚያነጻው እንዴት ነው?
5. እግዚአብሔር መከራ እንዲመጣ ለምን ይፈቅዳል?

መደምደሚያ

አሁን ትንቢተ ዘካርያስን ለማጥናት መልካም ጅማሬ አድርጋችኋል። ጥናታችሁን ላለመቋረጥ የሚረዳችሁ ዘዴ መጽሐፉን ለሌሎች ማስጠናት ነው። አንድ ሰው ወይም ቡድን ፈልጋችሁ የተማራችሁትን ነገር አካፍሉ። በዚህ ጊዜ ከመታካፍሏቸው ሰዎች ይልቅ እናንተ ብዙ እንደምትማሩ ትገነዘባላችሁ።